



## ሐዲሳን ኤጲስ ቆጶሳት በየሀገረ ስብከታቸው

# ትንሣኤ



ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን
የልማት ኮሚሽን የተገኘ ሥዕላዊ መግለጫ

ቁጥር 17 ፲፱፻፹፩ ዓ.ም.

www.ethiopianorthodox.org

"ይህ መጽሔት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፡ ሥርዓትና ዜና ፡ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጐምር እንዲተረ ጕሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ።

አዘጋጅ
ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅት
የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ
በሁለት ወራት አንድ ጊዜ
እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 116616
የመልእክት ሣ.ቁ. 3137
አዲስ አበባ

ማውጫ

| አርእስት | ገጽ |
| --- | --- |
| ደብዳቤዎች | ፩ |
| ቅዱስ ሲኖዶስ ስለጾም ምን ይላል ? | ፪ |
| ቃል ኪዳን በተግባር ሲገለጥ | ፫ |
| ብሩን ለምን ሰጠ ? | ፭ |
| የሃይማኖት ዓምድ | ፭ |
| ስለ ሸዋ ሀገረ ስብከት | ፮ |
| ምን እንርዳዎ ? | ፰ |
| የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ዜና | ፱ |
| ሐዋርያት ለተረሱ ሕዝቦች | ፲ |
| ሃይማኖት ያለ ምግባር | ፲፪ |
| መጽሐፍ ቅዱስና ልማት | ፲፫ |
| ዐሥራ ሦስት ኤጲስቆጶሳት | ፲፭ |
| የወንጌል አዳራሽ | ፲፮ |
| የሴቶች ዓምድ | ፲፯ |
| ሲኖዶስና ትርጉሙ | ፲፰ |
| የክርስትና እምነት እውነተኛነት | ፳ |
| ሥራ የተለየው ሕይወት | ፳፩ |
| ተክሊል ያለቁርባን ? | ፳፪ |
| ይህን ያውቁ ኖሯል ? | ፳፫ |
| እውነተኛ ጾም | ፳፬ |

# ደብዳቤዎች

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

በአካባቢዬ ካሉት ካህናትና ዲያቆናት እንዲሁም ከምእመናን ጋር በመነጋገር ማኅበረተኛ እንዲሆኑ ጋብዣቸው ነበር ነገር ግን 2 ምክንያቶች አሉባቸው 1ኛ የመጽሔቱም ሆነ የጋዜጣው ፍሬ ከዘመኑ ጋር የሚራመድ ካልሆነ በእምሮ ውስጥ ጦርነት መፍጠር ነው ይላሉ ይህን የሚሉት ተራማጅ እንሆናለን የሚሉ የአፍ ክርስቲያኖች ሲሆኑ በካህናትና ዲያቆናት አካባቢ የኢኮኖሚ ጉዳይ ችግር ሆኖባቸዋል ። ነገር ግን የኔን መጽሔትና ጋዜጣ እንዲያነቡ በመጋበዝ ስሜታቸውን በመቀስቀስ አባል ማኅበርተኛ እንደሚሆኑ ተስፋ አድርጌአለሁ ። የማይሰለቸኝ ቢሆን ከዚህ ቀደም በሬዲዮ ይሰጥ የነበረውን "ግእዝ በራዲዮ" የተባለውን በመጻጻፍ ለመሣተፍ ስለምሻ የሚቻል ቢሆን እባክዎ ከክፍሉ የቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣኖች ጋር ተነጋግረው የግእዝ ትምህርት የሚገኝበትን መንገድ ይፈልጉልኝ በተረፈ ስለ ትዕግሥትዎና ስለቅን አገልግሎትዎ እግዚአብሔር ይባርክዎ እግዚአብሔር ይስጥልኝ አመሰግናለሁ ። የመንፈስ ቅዱስ ወንድምዎ የክርስቶስ አገልጋይ

ወ ር አራጋው መኩሪያ
አድራሻዬ
ጨርጨር አውራጃ ሚኤሶ ወረዳ ፖሊስ
ሐረርጌ

ወ ር መኩሪያ ለክርስትና እምነት መስፋፋት ምን ያህል እንደሚጥሩ ተረድተናል ። ለጋዜጣችንና መጽሔታችንም ማኅበርተኛ በመሆንዎ እጅግ ደስ ብሎናል ።

ስለጋዜጣውና መጽሔቱ ከጊዜው ጋር አይራመድም የሚሉት አንዳንድ የክርስትና እምነት ምን እንደሆነ ያልገባቸው ናቸውና መጽሔቱና ጋዜጣው ሲደርስዎ ምን ዓይነት ጥቅም እንደሚሰጥ ያስረዷቸው ።

ከአሁን ቀደም በሬዲዮ ይተላለፍ የነበረውን የግእዝ ቋንቋ እፈልጋለሁ ላሉት እንልክልዎታለን ለማንኛውም ትብብርዎ አይለየን ።

★ ★ ★

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

1ኛ በኢትዮጵያ ውስጥ ስንት አብያተ ክርስቲያናት አሉ ? በየትኛው ክፍለ ሀገር በብዛት ይገኛሉ ? በብሉይ ዘመን በኢትዮጵያ ቤተ መቅደስ ነበር ወይ ? በየትኛው ክፍለ ሀገር ነበር ? በሐዲስ ኪዳንስ በየትኛው ክፍለ ሀገር ቤተ ክርስቲያን ታነፀች ?

2ኛ ወደ ቤተ ክርስቲያን በጫማ መግባት ይገባል ወይ ?

3ኛ ተክሊል ያለ ቁርባን ይገባል ወይ ?

4ኛ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅት ትንሣኤ መጽሔትን ብቻ ነው የሚያዘጋጀው ?

ወ/ት ተስፋነሽ ገ/ጊዮርጊስ
ተ.ግ.ግ. ፖ.ሣ.ቁ. 31238
አዲስ አበባ

ወይዘሪት ትስፋነሽ ስለ ጥያቄዎችሽ እያመሰገን መልሱን እንደሚከተለው እናቀርባለን ።

1ኛ በኢትዮጵያ ውስጥ 20.000 የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ ። በብዛት የሚገኘው በትግራይ ክፍለ ሀገር ነው ። በብሉይ ኪዳን ዘመን በትግራይ ክፍለ ሀገር በአክሱም አሪታዊ ቤተ መቅደስ ነበር በሐዲስ ኪዳን ዘመንም ለመጀመሪያ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን የታነጸች በአክሱም ነው ።

2ኛ እንደ ልማዳችን ወደቤተ ክርስቲያን በጫማ መግባት አይገባም ። የሚገቡ ቢኖሩ በድፍረታቸው ነው ።

3ኛ ተክሊል ያለ ቁርባን ሲፈጸም አይገባም ። እርግጥ አንዳንድ ሰዎች ሲፈጽሙ ይታያሉና የቤተ ክርስቲያናችን ሕግ አይደለም ።

4ኛ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅት የሚያዘጋጀው ትንሣኤ መጽሔትን ብቻ ሳይሆን ድምፀ ተዋሕዶ ጋዜጣን ያዘጋጃል መንፈሳውያን መዝሙሮችንና ትምህርቶችን በካሴት እየቀረፀ ለምእመናን ያቀርባል ። በእሑድና በበዓላት ቀኖች በከተማና በገጠር እየዞረ ወንጌልን ያስተምራል ። ከዚህም ጋር ት/ቤቶች አሉት ።

# ዐሥራ ሦስት . . .

ከገጽ ፲፭ የዞረ

ዲስ አበባ አድባራትና ገዳማት ፣ የካህናት ማኅበር ፤ የወጣቶች አጠቃላይ ጉባኤ አባላት ጥሪ የተደረገላቸው የልዩ ልዩ አብያተ ክርስቲያናትና የሃይማኖት መሪዎች ተገኝተዋል ። በእምነት ፣ በባ



ቅዱስ ፓትርያርኩ ከ13ቱ ሐዲሳን ኤጲስ ቆጶሳትና ከሌሎቹም ጳጳሳት ጋር

ህልና በዘመን ጥንታዊትነት ያላት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መሠረተ እምነትዋን ሳትለቅ በእነዚህ ብፁዓን ጳጳሳት ታላቅ ለውጥን እንደምታገኝ ተስፋ እያደረግን ሹመቱ ለመልካም ሥራ ፤ ለቤተ ክርስቲያንም እድገት ይሁንላቸው እንላለን ።



www.ethiopianorthodox.org

ርእሰ አንቀጽ

# ቅዱስ ሲኖዶስ ስለጾም ምን አስተያየት አለው ?

ቅዱስ ሲኖዶስ ስለጾም የሚሰጠውን መመሪያ ከመናገራችን በፊት ጾም ማለት ምን ማለት እንደሆነ ማወቅና መረዳት ሳይጠቅመን አይቀርም ።

ሶስት መቶ አሥራ ስምንት ሊቃውንት በደረሱት ፍትሐ ነገሥት ተብሎ በተሠየመው የሕግ መጽሐፍ አንቀጽ 15 ላይ ጾም ማለት ምን ማለት እንደሆነ ለምን አገልግሎት እንደሚጠቅም በብዙ መንገድ ተንትኖ ያስረዳል ።

ይኸው መጽሐፍ ሲያብራራ ጾም ማለት በታወቀው ዕለት በታወቀው ሰዓት ሰው ከምግብ የሚከለከልበት ወቅት ነው ይልና ይህንኑ በተጨማሪ ሲያብራራ በታወቀው ዕለት ያሉት ሰባቱ አጽዋማት ናቸው እንዲሁም በታወቀው ሰዓት ማለት ዓርብና ረቡዕ እስከ 9 ሰዓት ጾመ ሕርቃልን እስከ 12 ሰዓት ዓቢይ ጾምን ከቅድስት ሰኞ ጀምሮ እስከ ኒቆዲሞስ ዓርብ 11 ሰዓት ሰሙነ ሕማማትን 13 ሰዓት ከምሽቱ 1 ሰዓት ጨምሮ መጾም ይገባል ይላል ።

ስለጾም ጥቅምና ስለሚያስፈጽመውም ግዳጅ ሲናገር የጾም ጥቅም አንደኛ የፈቲውን ፃር ለማዳከም ሁለተኛ ምድራዊ ሥጋ ለለባዊት ነፍስ እንዲታዘዝ ነው ይላል ።

በእነዚህ በተወሰኑትም ጊዜያት ደም የሚወጣው የእንስሳ ሥጋ አይበላባቸውም በዘር በሩካቤ የሚወለድ፣ ከእንስሳት የሚገኙ ቅቤ ወተት እንቁላልና የመሳሰሉትም አይበሉም ፤ በተጨማሪም በዘር የሚበዙ እንስሳት ከእንስሳት ወገን ያይደሉ ፤ ያለ ዘር የሚበዙ ዓሣት በጾም ወራት መበላት እንደማይገባቸው መጽሐፉ ያወግዛል ።

ቅዱስ ሲኖዶስ ምጽዋት የገንዘብ ግብር እንደሆነ ጾምም የነፍስ ግብር መሆኑን ያጠይቃል በተጨማሪም ማንኛውም ክርስቲያን እንዲጾማቸው የተወሰኑትን አጽዋማት በዝርዝር የገለጻቸው ስብከት ገሃድ ዓርብና ረቡዕ ነነዌ ዓቢይ ጾም ጾመ ሐዋርያት ፍልሰታ ናቸው እነዚህን ሰባት አጽዋማት ማንኛውም ክርስቲያን የመጾም ግዴታ እንዳለበት ሐዋርያት በተናገሩት በመጀመሪያው ቀሌምንጦስ አንቀጽ 38 በትዕዛዝ 40 ላይ ፍትሕ ነገሥት አንቀጽ 15 በሰፊው ተብራርቶ ተጽፏል ።

በተለይ ዓቢይ ጾምንና ዓርብና ረቡዕን እንደቤተ ክርስቲያን ሕግ የማይጾም የቤተ ክርስቲያን አባል ቢገኝ ካህን የሆነ እንደሆነ ከሹመቱ ይሻር ፤ ሕዝባዊ ቢሆን ደግሞ ከቤተክርስቲያን አባልነት ይለይ ፤ ይላል ሲኖዶስ ትዕዛዝ 47 ።

በሌላ በኩል ደግሞ በጾም ወራት ማንኛውም ሰው መብላት አይገባውም ይልና የፀነሰች ነፍሰ ጡርና በሽተኛ ሁለቱ አይጹሙ ይብሉ ሁለተኛም በመንገድ ላይ ያለ በመርከብ ላይ ወይም በሌላ ነገር የሚጓዝ ተሳስቶ ቢበላ ከጾሙ ማለቂያ በሚቀጥሉት ዕለታት ጾሞ የቀረበትን ሕጋዊ ጾም ያስተካክል ይላል ።

ይህንን የቅዱስ ሲኖዶስን ቃል በማስመልከት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የካቲት 26 ቀን 1970 ዓ.ም. በዓቢይ ጾም (ድራር) ማታ በመገናኛ መሣሪያ ለመላው ሕዝበ ክርስቲያን ባስተላለፉት ቃለ ምዕዳን ላይ የሀገራቸውን ዳርና ድንበር ለማስከበር በጠረፍ የሚገኙ የጦር ሠራዊቶችና በደዌ ላይ የሚገኙ በሽተኞች ያገኙትን እንዲመገቡ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን የምትፈቅድ መሆኗን ሲናገሩ ሐሳቡም በቅዱስ ሲኖዶስ የተደገፈ መሆኑን ገልጸዋል ።

ስለዚህ ከላይ እንደተገለጸው ጾም ሥጋን ለነፍስ ለማስገዛት የሚያስችል መንፈሳዊ መሣሪያ በመሆኑ በደዌ ከተጨነቁና ስለሀገራቸውና ስለወገናቸው ክብር ሲሉ በጠረፍ ከሚገኙ ሠራዊቶች በስተቀር ሁሉም በሕብረት ሊጾመው ይገባል ጾም በሚጾምበት ጊዜ ትዕግሥትን ምጽዋትን የመሳሰሉትንም ሥነ ምግባራት ለማዳበር መልካም አጋጣሚ ይሆናል ።

አፍን ክፉ ከመናገር ገትቶ ፤ ዓይንን ክፉ ከማየት መለስ አድርጎ ፤ እግርን ወደ ክፉ ቦታ ከመሄድ ከልክሎ ፤ በልቡና ቂምንና በቀልን ከመያዝ ተወግዶ መጾም ክብርን የሚያጐናጽፍ መሆኑን አምነን መጾም ለክርስቲያኖች ሁሉ ግዴታችን ነው ። ቅዱስ ሲኖዶስም የሚያስተምረን በጾም መሣሪያ ሥጋዊና መንፈሳዊ ጠላቶቻችንን ድል ማድረግ እንድንችል ነው ።



# ቃል ኪዳን በተግባር ሲገለጥ

ከእጅጉ ረታ

በሥጋዊውም ሆነ በመንፈሳዊ ረገድ ሁለት ወገኖች በመካከላቸው ፀንቶ ሊኖር ስለሚገባው ግንኙነት የሚያደርጉት ውል ወይም ስምምነት ቃል ኪዳን ተብሎ ሊተረጐም ይቻላል ።

በመሠረቱ ቃል ኪዳን በተዋዋይ ወገኖች መካከል የተጠበቀ ሲሆን ረብ ጥቅም የሚገኝበት ሳይጠበቅ ቢቀር ያፈረሰው ወገን በኃላፊነት የሚጠየቅበት መሆኑ የታወቀ ነው ።

መቼም በሰዎች መካከል የሚደረግ ውል ወይም ቃል ኪዳን ዞሮ ዞሮ በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረተ ስለሚሆን ግዴታን ማስከተሉ በየዘመናቱ ሁሉ በተግባር ተገልጦ ታይቷል ። በዚህም አንጻር በእግዚአብሔርና በመጀመሪያው ሰው አዳም መካከል የነበረው ግንኙነት ከዚህ የተለየ ሆኖ አይታይም ። ለአባታችን ለአዳም ምርጫን ለመወሰን የሚያስችል ውዴታም ግዴታም ያለበት ነፃ ፈቃድ ተሰጥቶት ነበር ። ዳሩ ግን ይህን የነፃ ፈቃድ መለኪያ የሆነውን ሕግ በተግባር ሊገልጠው ባለመቻሉ ተፈርዶበት ከመርገምና ከፍዳ በታች ሊወድቅ በቅቷል ። ከዚህም የተነሣ ስላዘነና ስለተፀፀተ አምላክ በሥጋ ለመገለጥና በመስቀል ላይ ሞቶ የበደሉን ዕዳ በደሙ ለመካስ ፈቃዱ ሆነ በዚህም መደበኛው የምሕረት ቃል ኪዳን የተፈጸመ መሆኑን ቅዱሳት መጻሕፍት ያረጋግጣሉ ።



ድንግል ማርያም የምሕረት ኪዳን ስትቀበል

ክቡር ዳዊት ሁሉም ተስተካክለው በደሉ መዝ. 13.3 ፣ እንዳለው የሰው ልጅ ከኃጢአት የተለየበት ፣ ከክፉ ሥራው የተገታበት ጊዜ እንዳልኖረ ግልጽ ነው ። ይህም ሆኖ የእግዚአብሔር ይቅርታና ምሕረቱ ደግሞ በዚያው መጠን የተትረፈረፈ ሆኖ እናገኘዋለን። ይህንንም በሚቀጥሉት ሁኔታዎች ለመረዳት ይቻላል ።

እነሆ በብሉይ ኪዳን ዘመን ......ለሚወዱት ትእዛዙንም ለሚጠብቁ ቃል ኪዳኑንም ምሕረቱን እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ የሚጠብቅ የታመነ አምላክ እንደሆነ ተጽፏል ። (ዘጸአት ም. 34 ቁጥር 7) ይህም የልዑል እግዚአብሔር ፈቃድ ይበልጥ የሚያመዝነው ለይቅርታና ለምሕረት መሆኑን ያስገነዝበናል ።

በሌላም አንጻር ስንመለከተው በያለኞችን እርሱ ራሱ ባለቤቱ በቀጥታ ይቅር ሊላቸውና ሊምራቸው ሲችል ፣ የቅዱሳን ወዳጆቹ ባለሟልነትና ክብር እንዲገለጥ የሚፈልግ መሆኑ በቅዱሳት መጻሕፍት በብዙ ቦታ ተጽፎ እናገኛለን ። ይህም ባጭሩ አብርሃም ለአቤሜሌክ ፣ ኢዮብ ለኤሊፋዝና ለሁለት ባልንጀሮቹ እንዲጸልዩላቸው በማዘዙ ይታወቃል ። (ዘፍ. ም. 20 ቁ. 7 እና 17 ኢዮብ ም. 42 ቁጥር 7 - 10)

የእግዚአብሔር ወዳጅ ሙሴም፣"አባክህ ፣እንደ ምሕረትህ ብዛት የዚህን ሕዝብ ኃጢአት ይቅር በል" በማለት በማለደ ጊዜ እንደ ቃልህ ይቅር እላለሁ በማለቱ ከመረጥሁት ጋር ቃል ኪዳን አደረግሁ ያለውን ቃሉን እንደ አጸና እንረዳለን ።

ይልቁንም ጌታ በወንጌል "በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል" ሲል አስተምሯል ። (ዮሐ. 14 ቁጥር 12) ይህም ለቅዱሳን የተሰጣቸው የአማላጅነትና የገቢረ ተአምራት ሥራ በየጊዜው በተግባር ሲገለጥ ታይቷል ።

ታዲያ ይህን የመሰለ ባለሟልነትና



www.ethiopianorthodox.org

ክብር ለወዳጆቹ የተሰጠ ከሆነ አባትህንና እናትህን አክብር ብሎ ያዘዘ አምላክ ለእናቱ ለቅድስት ድንግል ማርያም የሰጣት ጸጋና ክብር የቱን ያህል ብልጫ ያለው መሆኑን መገንዘብ አያቅትም በዚህም እመቤታችን ቅ ድንግል ማርያም ከልጅዋ በተቀበለችው ቃል ኪዳን መሠረት ያደረገቻቸው ድንቅ ሥራዎች ሥፍር ቁጥር እንደሌላቸው የታወቀ ነው ። ከዛሬ 500 ዓ. ም. በፊት በተጻፈው የተአምረ ማርያም መጽሐፍ ተጠናቅረው የምናገኛቸውም ቢሆኑ በመካከለኛው ምሥራቅና በአካባቢው ያደረገቻቸውን ተአምራት ቢያወሱ እንጂ በመላው የክርስትና ዓለም የተደረጉትን ሁሉ ሙሉ በሙሉ የሚያጠቃልሉ ናቸው ለማለት አይቻልም ።

የእግዚአብሔር ቸርነት ፣ በተሰጣቸውም ጸጋ የቅዱሳን አማላጅነትና ገቢረ ተአምራት ከሚታወቁባቸው ሁኔታዎች አንዱ ፀበል መሆኑ በተግባር ሲገለጥ በየጊዜው ታይቷል ፣ አሁንም ይታያል ።

ዛሬ የሳይንስ ምርምርና ጥናት ከፍተኛ ደረጃ ላይ በደረሰበት ባሁኑ ወቅት እንኳ ፣ የሕክምና ጥበብ ገና መፍትሔ ሊያገኝላቸው ያልቻለ ፣ ከባድና ተስፋ የሚያስቆርጡ ሕመሞች በሃይማኖት ኃይል ድል እንደሚመቱ ተረጋግጧል ። ለሚያምን ሁሉ ይቻለዋል ተብሏልና ።

እንደ ሚጣቅ እንደ ደብረ ሊባኖስና እንደ ወሊሶ ባሉት መንፈሳውያን ቦታዎች በእምነት ኃይል የሚፈጸሙትን ሁሉ እስፍራው ተገኝቶ ባይኑ ላላየ ሰው ቢነግሩት እውነት ላይመስለው ይችላል ።

በሀገር መድኃኒት ታክተው በሕክምናም ተስፋ ቆርጠው ያበቃላቸው መሆኑን ከተረዱ በኋላ እንጦጦ ኪዳነ ምሕረት ወጥተው በቃል ኪዳኗ ተማጽነውና በጽኑ ልብ አምነው በጸበሏ በመጠመቅና በመጠጣት የዳኑት ሰዎች ብዛት በውል ተመዝግቦ ስለማይገኝ በትክክል ለማወቅ አይቻልም ። ሥፍር ቁጥር የለውም ።

እዚህ ላይ ለእኔ ለራሴ የተደረገልኝና ለሌሎችም ሲፈጸም በዓይኔ ያየሁትን የእምቤታችንን ተራዳኢትነት ሳልገልጠው አላልፍም በ1969 ዓ.ም. ለሞት በሚያደርሰው ጽኑ ደዌ ተይዤ ሆስፒታል ገብቼ ነበር።ሁለት ወር ሙሉ ሳልገላበጥ በጀርባዬ ብቻ ተንጋልዬ እንድተኛ በመደረጉ ያሳለፍኩትን ሕማምና ስቃይ ሳስታውሰው አሁንም ይዘገንነኛል።ታዲያ በመጨረሻ በተገኘው ምርመራ ውጤት መሠረት የተሰጠኝ የሕክምና ማስረጃ በሕይወተ ሥጋ ብቆይም ባልቆይም ዋጋ እንደሌለኝ የሚያስረዳ በመሆኑ በጆሮ ግንዴ ይሰማኝ የነበረው ድምፅ እንግዲህ ያንተ ነገር እኮ አከተመ አብቅቶልሃል የሚል ነበር ። ታዲያስ ራሴን ጠየቅሁት አንድ ተስፋ ብቻ ነበረኝ ይኸውም የሃይማኖት ኃይል ነበር ፣ ከዚህም የተነሣ በእመቤታችን ተራዳኢትነት አምኜ በእናትነቷ ተማጽኜ በጸሎትና በእንባ ተጠምጄ ለሰባት ዕለታት በጠበሏ ደተጠመቅሁ በኋላ እዚህ ላይ ለጊዜው ልገልጠው የማልፈልገውን ምልክት አግኝቼ ጤንነቴ እንዳለ ተመልሶልኝ ይኸው አለሁ ። ባጭሩ በቀጠሮዬ ለምርመራ ተመልሼ በሄድኩበት ወቅት ሐኪሙ ዓይናቸውን ሊያምኑት አልቻሉም ። “አንተ ነህ ወይስ ሌላ ሰው” አሉ ፤ ሰው በዕውቀቱ ፍጹም እንዳይደለ ከተረዳሁ ቆይቻለሁና ቢያስደንቃቸው አልገረመኝም።ለሌሎቹ ከተደረጉት የምሕረት ሥራዎች ደግሞ 1ኛ ከዚሁ ከአ አበግምት 27 ዓመት ዕድሜ ያለው ወጣት ሁለት ዓመት ሙሉ በአእምሮ ሕመም (መታወክ) ምክንያት በአማኑኤል ሆስፒታል ሲታከም ቆይቶ ሊድን ባለመቻሉ ወላጆቹ አምጥተውት በዚሁ ጠበል ተጠምቆ ምን እንደለፈለፈ መስማቱና መዳኑን አይቼ ለመመስከር በመብቃቴ 2ኛ/ አንዲት በግምት 18 ዓመት የሚሆናት ወጣት ወገቧ እንደደጋን ጎብጦ እግርና ራሷ ተጠግቶና ተኰራምታ እናቷ ከደሴ ከተማ አምጥተው በዚያም በዚህ ቢሉ የማይሳካ ሆኖ በዚሁ ጠበል ተጠምቃ መፈወሷ ለምንጊዜውም የማይረሱኝ ናቸው ።

በመላእክት ድርሳናትና በጻድቃንና በሰማዕታት ገድል ፣ በተአምረ ማርያምም መጻሕፍት ተመዝግበው የምናገኛቸው አስደናቂ ታሪኮች ተረትና መሠረት የለሾች ናቸው ብለን የምናስብ ብንኖር ሳንመረምርና ሳንረዳ እንዳንሳሳት መጠንቀቅ ይኖርብናል ። ለእግዚአብሔር ምን የሚሳነው ነገር አለ ? ዛሬም ቢሆን በእውነቱ የቅዱሳን ወገኖችን አሠረ ፍኖት ተከትለን ጌታን እነርሱ ደስ እንዳሰኙት እኛም ደስ ብናሰኝ ለእነርሱ የተሰጠው ጸጋና ክብር ለእኛ የማይሰጥበት ምክንያት ያለ አይመስለኝም

በዚህ አጋጣሚ ያለፉት አባቶቻችን ትጉሆች ታታሪዎች ስለሆኑ በየዘመናቱ የተደረጉትን አስደናቂ ነገሮች ሁሉ ጽፈው ስላቆዩን ግዴታቸውን ተወጥተው ማንነታቸውን በተግባር ገልጠው አልፈዋል ። በዚህም ልናመሰግናቸው ይገባናል ።

እኛም ብንሆን ያለፈውን ብቻ ማውሳት ሳይሆን በተግባር የተገለጠ ሥራ ለተከታዩ ትውልድ ማቆየት አለብን ። ከእነዚህም አንዱ በእግዚአብሔር ቸርነት በእመቤታችን ተራዳኢትነትና በቅዱሳን አማላጅነት በየጊዜው የሚፈጸሙትን ድንቅ ሥራዎች እየተከታተሉ በትክክል መዝግቦ ማቆየት ስለሆነ ቤተ ክርስቲያናችን ልታስብበት ይገባል ።



# ብሩን ለምን ሰጠ ?

አታላይነት የመረዘው ፣ በተንኰል የሠለጠነ ሰው ምን ጊዜም ቢሆን ሹመትን ለመግዛት ብሩን ይሰጣል ። ይህ የሰላም ጠላት የኅብረት ጠንቅ የሆነ የአመጽ ግብር ፈጻሚና ተከታዩ ሁሉ በጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን መሪዎችና መምሪያ ቦታ የለውም ተቀባይነትም አያገኝም ነበር ። ምክንያቱም ሰብስቦ የሚያቀርበው ብር ሠርቶ በማትረፍ በእውነተኛ አገልግሎት ያገኘው ንጹሕ ገንዘብ ሳይሆን በሐሰትና በአታላይነት ፣ መስሉ ከሆነ አታላይ እየተስማማ በማታለል ከሕዝቡ ሰብስቦ ራሱን የጠቀመ መስሎት ስሕተቱን አስፋፍቶ ወገኖቹን የሚጐዳበት ነው ። ይህም የማታለል ዘዴ በአሠራሩ ብዙ ክፍሎች አሉት ይኸውም በሰላም ተባብሮ የሚኖረውን ሕዝብ አሳስቶና አጣልቶ እያለያየ በልዩ ልዩ አስመሳይ ዘዴ ሀብቱን የሚሰበስብበት ነው ። ይህም የስንፍናና የአመጽ ግብር ፈጻሚ ግብሩ በረቀቀ አስመሳይ ዘዴ በየጊዜው እየተስፋፋ ሄዶ በየመሥሪያ ቤቱ እየገባ ሠራተኛውንም በሐሳብ እንዲለያይ የሚያደርግ ነው።

ዓላማውም በጐሣ በቋንቋ በወንዝ በሃይማኖታዊ የስም ብዛት በቀለም ልዩነት እየተከተለ በየክፍሉ እንደሚታወቀው ሁሉ ማለያየት ብቻ ሳይሆን በረቀቀ ነገር ብዙ ጉዳትንም ያደርሳል። ውጤቱም በእስተዋይነት ለተመለከተው ሰውን ከሰው እያለያየ ጥቅሙን ብቻ የሚሰበስብ ከመሆኑም በላይ ለሰው የማይራራ አስመሳይ ተንኰለኛና ጨካኝ ሁኖ ይገኛል ። ይህም አጥብቀን በመመርመር በየክፍላችን ተባብረን ልናስወግደው የሚገባን የጠላት መሣሪያ ነው ። በምርመራውም ጊዜ በቀላሉ የምንረዳበት መሣሪያ ይህ የወገንን ስም ተጠግቶ ብሩን በመስጠት ልዩነትን የሚፈጥር አስመሳይ ተንኰለኛ ወገኖቹ የሆኑትን ሁሉ አስተካክሎ ይመራልን? ብለን ብንጠይቅ በፍጹም አስተካክሎ አይመራም ።

ይህንም ለማወቅ ከተፈለገ ከመቶ ዘጠና ስምንቱን ድሆች ወገኖቹ አስወግዶ ከ100 ሁለቱ ብር የሚያቀርቡ ሁነው ከተገኙ በእውነተኛው ወገንነት ሳይሆን በግብር የሚተባበሩትን ብቻ ይዞ ሲበዘብዝ እንደሚገኝ አያጠራጥርም ።

ሁኖም እንደ ጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን አመራር የተከተለ እውነተኛ መርማሪና ወሳኝ ያስፈልጋል ። በእውነት ተመርምሮ ካልተለየ ግን እውነተኞች አባቶችና ካህናት እንዲሁም ታታሪዎች ሠራተኞች ባላወቁትና ባልሠሩት ሥራ ያስነቅፋቸዋል ። ከዚህ ላይ ትምህርቱን ለማሳጠር የቤተ ክርስቲያን ዓላማ በመሠረቱ ዕድገት በኅብረት ነው ። ማቴ. 18፥19-20 አሁን በዘመናችን እልፎ አልፎ የሚታየው ግን እውነተኛውን የቤተ ክርስቲያን ሕግ የተከተለና የጠበቀ መስሎ አይታይም ። ምክንያቱም በየአድባራቱና በየመሥሪያ ቤቱ የሚታየው ብጥብጥ ሲመለከቱት በእውነትም ሕጉን አልተከተለም ለማለት ያስደፍራል ። ይህንንም መዝኑን ለመረዳት እንችል ዘንድ ቤተ ክርስቲያን በተመሠረተችበት ጊዜ አብሮ የተመሠረተው የባለሥልጣን አመራርና ውሳኔ እንዲህ ይላል ።

ሲሞን የሚሉት አንድ የወገኑን ሀብት በማታለል የሚዘርፍ እኔ ታላቅ ነኝ ብሎ እየጠነቆለ የሰማርያንም ወገን እያስገረመ ሕዝቡ ሁሉ ታላቁ የእግዚአብሔር ኃይል ይህ ነው እያሉ ያዳምጡት ነበር ። ከብዙ ዘመንም ጀምሮ በጥንቆላ በላስገረማቸው ያዳምጡትና ይታዘዙለት ነበር ። ነገር ግን ስለእግዚአብሔር መንግሥትና ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም እየሰበከላቸው ፊልጶስን ባመኑት ጊዜ ወንዶችም ሴቶችም ተጠመቁ ። ሲሞንም ደግሞ ራሱ አመነ ተጠምቆም ከፊልጶስ ጋር ይተባበር ነበር ፊልጶስ የሚያደርገውንም አምላካዊ ምልክትና ታላቅ ተአምራት ባየ ጊዜ ተገረመ ። በኢየሩሳሌምም የነበሩት ሐዋርያት የሰማርያ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል እንደተቀበሉ ሰምተው ጴጥሮስንና ዮሐንስን ሰደዱላቸው እነርሱም በወረዱ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ይቀበሉ ዘንድ ጸለዩላቸው ። በጌታ በኢየሱስ ስም ብቻ አምነው በራሳቸው ተጠምቀው ነበር እንጂ በሐዋርያት እጅ አልተጠመቁምና ከእነርሱ በአንዱ ላይስንኳ ገና መንፈስ ቅዱስ አልወረደም ነበር በዚያን ጊዜ ሐዋርያት እጃቸውን ጫኑባቸው መንፈስ ቅዱስንም ተቀበሉ ሲሞንም በሐዋርያት እጅ መጫን መንፈስ ቅዱስ እንዲሰጥ ባየ ጊዜ ገንዘቡን አመጣላቸውና እጄን የምጭንበት ሁሉ መንፈስ ቅዱስን ይቀበል ዘንድ ለእኔ ደግሞ ይህን ሥልጣን ስጡኝ አለ ።

በቤተ ክርስቲያንም በሲሞን ያደረ ሰይጣን የጉቦ ሰጭና ተቀባይ መገናኛ የሆነ የብዝበዛ መርዙን ተከለባት ። ከዚህ ላይ ነው ብሩን ለምን ሰጠ ለሚለው ጥያቄ መልሱ ሹመትን በጉቦ ለመግዛት ነው ብሎ ለማስረዳት የሚቻለው ። ስለዚህ ምንጊዜም ቢሆን በጐሣ ስም ተጠግተው በልተህ አብላኝ በሚል ግንኙነት ብቻ የሕዝቡን ሀብት የሚበዘብዙ ሁሉ የሲሞን ግብር ተከታዮች ናቸው እንጂ እውነተኛው የቤተ ክ ክርስቲያን ሕግ ጠባቂዎች አይደሉም ።

ማስረጃውም ሲሞን ብሩን ሰጥቶ ሹመት ስጡኝ ባለ ጊዜ እውነተኛው የቤተ ክርስቲያን መሠረትና ሕግ ጠባቂ የሆነው ቅዱስ ጴጥሮስ እንዲህ አለው ። የእግዚአብሔርን ስጦታ በገንዘብ እንድታገኝ አስብሃልና ወርቅህና ብርህ ከአንተ ጋር ይጥፋ ። ልብህ በእግዚአብሔር ፊት የቀና አይደለምና ከዚህ በረከት ዕድል ወይም ፈንታ የለህም ። እንግዲህ ስለዚህ በክፋትህ ንስሐ ግባ በማለት አስተምሮና መክሮ ስለ ሁኔታውም አብራርቶ በመራራ መርዝና በዓመፅ እስራት እንዳለህ አይሃለሁና ንስሐ ግባ ብሎታል የሐዋ.8፥9-24 ሲሞንም ከዚህ መራራ የሆነ ውድቀት የጣለው ከማመኑ በፊት ሲፈጽመው የነበረው አታላይነት ብቻ አይደለም ።

ከአመነና ከተጠመቀ በኋላ በመጽሐፍ ቅዱስ ጉቦ መስጠት የተከለከለውን በመተላለፉ ነው ። ይኸውም ማማለጃን አትቀበል ። ማማለጃ የዓይናማዎችን ሰዎች ዓይን ያሳውራልና የጻድቃንንም ቃል ያጣምማልና የሚለው ነው ዘጸ. 23፥8-9 ይህ ከዚህ በላይ የተመለከትነው ማስረጃ የጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን እውነተኛ መምሪያ ነው ። አሁንም ሕጉ አልተሻረምና ከሥራ ላይ መዋል አለበት ። ምክንያቱም በዘመናችን እንደምንሰማው የብዙኃኑ ሕዝብ ገንዘብና የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች የሆኑ የጭቁን ካህናት ድርሻ የሆነውን ገንዘብ አንዳንድ ብልጣብልጦች ያለ አግባብ አጥፍተው ሲከሰሱ ክሱ ሳይጣራና ውሳኔ ሳያገኝ እንዲቀር የሚያደርጉት ብር ሰጪና ተቀባይ ናቸው ለማለት ያስደፍራል ። እነዚህ ብር ሰጭና ተቀባይ ተስማምተው የሚፈጽሙት በደል ሲመዘን ደግሞ ሲሞን ከፈጸመው አመጽ በላይ ስለሆነ ዘመናችንና ቅዱስ መጽሐፋችን አይደግሙ.ውምና በሞያችንና በሥራችን እንጠቀም ።



የሃይማኖት ዓምድ

# ሀላዌ እግዚአብሔር

የነገረ መለኮት ተመራማሪዎች የእግዚአብሔርን ህላዌ ለማስረዳት ከሚጠቀሙባቸው አምስት ያህል የፍልስፍና ትምህርቶች መካከል ሁለት ያህሉን ባለፉት ተከታታይ ቁጥሮች አትመን ማውጣታችን ይታወሳል ። በአሁኑ እትም የምናየው ሐሳብ ደግሞ ፓንቴይዝም የተሰኘውን 3ኛ ክፍል ነው ።

ፓንቴይዝም ማለትም እግዚአብሔር ከዓለሙ የተለየ ሳይሆን ምሉእ በኲለሄ (ሁሉን በሁሉ) የሆነ ነው የሚል ሐሳብ የሚቀርብበት አመለካከት ነው ። እውነት ለመናገር ግን በዚህ ሐሳብ የሚቀርበው አባባል ፍጹም ነው ለማለት አዳጋች መሆኑን በቅድሚያ እየገለጥን ማስረዳት የምንፈልገው አጭር ነገር የሰዎችን በሐሳብ መለያየት (የአይዲዮሎጂ ልዩነት) ወይም የእግዚአብሔርን

መምህር ኪዳነ ማርያም ገ/ሕይወት

www.ethiopianorthodox.org

# ስለ ሸዋ ሀገረ ስብከት ከቀሲስ ሰሎሞን ጋር

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከሰውጡ ወዲህ በበለጠ እንድትስፋፋና ስብከተ ወንጌልም ባልደረሰባቸው ለማዳረስ በክፍለ ሀገር በአውራጃና በወረዳ ደረጃ የሰጠኣ ጉባኤን በማቋቋም ላይ ናት ።

ይኸውም ምእመናን በያዙት ሃይማኖት ጸንተው እንዲኖሩ ቀሳውስትና ዲያቆናትም በተለያዩ ሰሚናሮች እየሰለጠኑ እንዲነቁና እንዲደራጁ ለማድረግ ነው ።

ቀሳውስትና ዲያቆናት ከነቁና ከተደራጁ ምእመናንን በሚገባ ስለሚያስተምሯቸውና የቤተ ክርስቲያንን ሕግ ስለሚያስጠኑዋቸው ሁለቱ ማለት ቀሳውስትና ምእመናን ተዋሕደው የቤተ ክርስቲያንን ዕድገት ከፍ ለማድረግ ይችላሉ ተብሎ ይታመናል ።

ስለዚህ ሁኔታ ማብራሪያ እንዲሰጡን የሸዋ ሀገረ ስብከት ዋና ሥራ አስኪያጅ መምህር ሰሎሞን ገብረ ሥላሴን ጠይቀናል ።

<u>ትንሣኤ</u> ፦ ቤተ ክርስቲያናችን ራስዋን በራስዋ እንድታስተዳድር ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት መብት ሰጥቷታል በዚህም መሠረት ቤተ ክርስቲያን ራስዋ (በሰበካ ጉባዔ) እንድትመራበት ቃለ ዓዋዲ አውጥታለች ስለዚህ በሸዋ ክፍለ ሀገር የተቋቋመው የሰበካ ጉባዔ እንዳለና ምን ያህል እንደተጠቀመበት ቢያብራሩልን?

<u>መምህር ሰሎሞን</u> ፦ በሸዋ ክፍለ ሀገር ሀገረ ስብከት ያሉት አውራጃዎች 11 ሲሆኑ በዚህ አውራጃ ውስጥ ከሁለት ሺ ሰባት መቶ በላይ የሚሆኑ አብያተ ክርስቲያናት ኀንዳሉ መዝገባችን ይናገራል እንዲህ ሲሆን በእነዚህ አውራጃዎች የሰበካ ጉባኤ ያልተቋቋመበት ቦታ የለም ። በሁሉም የሰበካ ጉባኤዎች እየተጠናከሩ ናቸው። የሆነ ሁኖ የቀድሞ ጊዜ ሥርዓት ከርስት ጋር የተያያዘ ቃለ ዓዋዲ ስለነበረ መሬት ለአራሹ ከታወጀ ወዲህ ቤተ ክርስቲያን የራስዋን ንብረት የምትጠብቀው በስለት ፣ በሙዳየ ምጽዋት ፣ በምታገኘው ገንዘብ እንጂ ከርስት ጋር የነበራት ይዞት የተሰረዘ ስለሆነ ከዚያ ወዲህ ቃለ ዓዋዲ እንደገና እንዲዘጋጅ ተደርጓል ። ለምሳሌ በመጠኑ የደረሱንን እትሞች በየአውራጃው እየተዘዋወርን መግለጫ በመስጠትና በማስተዋወቅ ላይ እንገኛለን ። ለወደፊት ግን ለመላው በኢትዮጵያ ለሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ከ15 ሺ እስከ 20000 የሚሆን ቃለ ዓዋዲ እየታተመ ነው ያ ታትሞ በሚደርሰን ጊዜ 1ኛ በክፍለ ሀገር 2ኛ በአውራጃ 3ኛ በወረዳ በሶስት ምድቦች ሀገረ ስብከታቱን በሚገባ ለማጠናከር በመጠየቅ ላይ ናቸው እንዲያውም ካርድና ካርኔ የሚወስዱ ከዕለት ወደ ዕለት እየጨመሩ ሂደዋል ። ሀገረ ስብከቱም ይኸንን ለማጠናከር ያለ ዕረፍት እየሠራ ነው ።

<u>ትንሣኤ</u> ፦ በሸዋ ሀገረ ስብከት በርከት ያሉ ገዳማት እንዳሉና እነዚህም ገዳማት ራሳቸው ሳይሠሩ ከሌላው ግብር እየተቀበሉ ይተዳደሩ እንደነበረ የታወቀ ነው መሬት ለአራሹ ከታወጀ ወዲህ ግን በምን ዘዴ እንደሚተዳደሩ ቢገልጹልን?

<u>መምህር</u> ፦ አዎ በተለይ በሸዋ ሀገረ ስብከት ብዙ ገዳማት አሉ ለምሳሌ እነ ደብረ ሊባኖስና እሱንም የመሳሰሉት ገዳማት መኖራቸው የታመነ ነው ። መሬት ለአራሹ ከተሰጠ ወዲህ በምን ይተዳደራሉ ስለ ሚለው ጥያቄ መሬት ለአራሹ መስጠት ቤተ ክርስቲያናችን በጸጋ የተቀበለችው አዋጅ ነው ፣ መንግሥታችንም ይህንን በሚያውጅበት ጊዜ መሬት ለአራሹ አለ እንጅ መነኮሳት ቀሳውስት ዲያቆናት አያርሱ አላለም የኢትዮጵያ ምድር ለኢትዮጵያውያን ናት ይህ አዋጅ ማንም ኢትዮጵያዊ እርሶ እንዲያድር እንጅ ቄስ መነኩሴ ብሎ የለየበት አዋጅ የለውም ።

እርግጥ የገዳማት መሬት ለሰፊው ሕዝብ ሁኗል ፈትም ቢሆን የገዳማት መሬት መኳንንት መሳፍንት በገዳማት ስም ይጠቀሙበት ነበር እንጅ ገዳማቱ አልተጠቀሙበትም ነበር በገዳም የሚኖሩ መነኮሳት ራሳቸው ቢያርሱ የመሬት ለአራሹ አዋጅ ባልጉዳቸውም ነበር ምክንያቱም አዋጁ አርሶ የሚያድረውን ሁሉ የሚያጠቃልል ነው ለወደፊቱም የሀገረ ስብከቱ ጽ ቤት ጉዞ ገዳማት እንዲስፋፉ መነኮሳቱ እንዲያርሱ ቤተ ክህነት ከአንዳንድ ድርጅቶች ገንዘብ እየጠየቀ መነኮሳቱ ገዳማቸውንና ቤተ ክርስቲያናቸውን እያገለገሉ እንዲኖሩ በመጣር ላይ ነው አሁን እንኳ ረሐብ አጥቅቷቸው ችግራቸውን ስለ ሰማን ባለፈው ዓመት ለደብረ ሊባኖስ ከአንድ ድርጅት ለምነን ለጊዜው የሚሆን ሶስት ሺ አምስት መቶ ብር ከአንዱም ሶስት መቶ ብር በጠቅላላው ሰባት ሺ ስምንት መቶ ብር ሰጥተናቸዋል እንዲሁም ጫጋል መድኃኔ ዓለም ለተባለው ገዳም ከ60 እስከ 70 ለሚሆኑ ድኩማን ከአንድ መንፈሳዊ ሰው ሦስት መቶ ብር እርዳታ አግኝተን ሰጥተናቸዋል ።

እንደገና ለመልሶ ማቋቋም ዋና መሥሪያ ቤት ኮምሽነር ሽመልስ አዱኛ እንዲያውቁት ተደርጎ ለዚህ ለጫጋል መድኃኔ ዓለም 300 ኩንታል በቆሎ እርዳታ ስለሰጡን ድኩማኑ ዓመቱን ሙሉ ቀለብ አግኝተው ሲመገቡ ከቆዩ በኋላ ስለአለቀባቸው እንደገና አምሳ ኩንታል በቆሎ ሰጥተውናል በዚህ አኳኋን ሕይወታቸው ተጠብቆ ቆይቷል ።

ግን በመለመን ብቻ የሚዘለቅ ስላልሆነ ራሳችሁ ልታለሙ ከቻላችሁ አንድ ጋሻ መሬት እንሰጣችኋለን በማለት የአብዮት ኮሚቴ ተሰብስቦ ቦታውን ከልሎ በደብዳቤ አረጋግጦልናል ይህንንም የቤተ ክህነት ጠቅላይ ጽ/ቤት የልማት ኮሚቴ እንዲያውቀው ጽፈን ስለነበር ከልማት ኮምሽን የበሬ መግዣ ገንዘብ እንደሚሰጥ የታወሰ መሆኑ ተገልጾልናል ።

ከዚህ ሌላ ስለ አጋት መድኃኔዓለም ለልማት ኮምሽን አመልክተን 3000 ሺ ብር እርዳታ ተገኝቶ ይህ 3000 ሺ ብር ተልኮ የሰላሌ አውራጃ ጽ/ቤት እህል እንዲፈቅድላቸው ደብዳቤ ጽፈን አስተላልፈናል ።

ለዝቋላም እስከ $15000ሺ ዋስትና የተሰጠ ሲሆን እስካሁን ድረስ 7000 ብር ናዝሬት በሚገኘው ባንክ ገቢ ሆኖ ከዚያ እያወጡ እህል እንዲሸምቱ ተደርጓል ።

ለምድረ ከብድ ገዳም ለክርስቲያናዊ ተራድኦ ጠይቀን $15000 ሺ ብር አግኝተን ለጊዜው $7000 ሺ ብር ፈቅዶአል ከዚያም ውስጥ 3000 ሺ ብር ወስደው እህል ሸምተዋል ።

ለደብረ ጽሙና ገዳምም ከክርስቲያናዊ ድርጅትና ከሌሎች ድርጅቶች በመለመን ለወደፊቱ



ቀሲስ ሰሎሞን የሸዋ ሀ/ ስብከት ሥራ መሪ

ወፍጮ እንዲቋቋምላቸው ለማድረግ ጥናት በማድረግ ላይ ነን ወፍጮው ሲቋቋም የገዳሙ ቀለብ በነፃ ከመፈጨቱም ሌላ በዙርያው ያለው ሕዝብ ሁሉ ከዚያው እያስፈጨ ገቢው ለገዳሙ ስለሚሆን አንድ ውጤት ያስገኛል የሚል ተስፋ አለን ።

አሁንም አረንጓዴ ዘመቻ እንዲደረግ በታወጀው መሠረት ቤተ ክርስቲያናችን የሰውን እጅ አይቶ ማደር ሳይሆን በወዝህና በላብህ እየሠራህ እንጀራህን ብላ ብሎ እግዚአብሔር በሠጠው አምላካዊ ትእዛዝ መሠረት ሠርተው እንዲያድሩ እቅድ አውጥተን የሥራውን ዘዴ በመግለጽ ራሳቸውን በራሳቸው ረድተው እንዲኖሩ ለማድረግ ሙሉ ትብብር በማድረግ ላይ ነን ።

<u>ትንሣኤ</u> ፦ በየቤተ ክርስቲያኑ ንዋየ ቅድሳት ጠፋ የሚል ድምፅ ይሰማል ስለዚህ ለወደፊት የቤተ ክርስቲያን ንዋያተ ቅድሳት በምን ዓይነት አጠባበቅ እንደሚጠበቁ የታቀደ እንዳለ ቢገልጹልን ።

<u>መምህር</u> ፦ በውነቱ በመላ ኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት ገባ ብለን ብንመለከት ንዋያተ ቅዱሳቱ በሚገባ ተጠብቀዋል ለማለት እንደፍርም የአጠባበቁ ጉድለት በውነቱ ብዙ ጊዜ እኔ ወደ ውጭ ሀገር ስለ ሄድኩ ለመገንዘብ ችያለሁ ምስክርነቱንም መስጠት እችላለሁ በምሥራቅ ሆነ በምዕራብ የብራና መጻሕፍት የቤተ ክርስቲያን ንዋያተ ቅድሳት በጠቅላላ የቤተ ክርስቲያናችን ቅርሳ ቅርሶች የነሙት የኒቨርሲቲና ሙዜሞችን እያሟሟቁና የእነሱን ሀብት እያበለጸጉ ናቸው በተለይ በእንግሊዝ በአሜሪካ በሶቪየት ሕብረት ፣ በፈላንድ ፣ በየቦታው ብንሄድ የኢትዮጵያ ንዋያተ ቅዱሳት ያልተከማቹበት ሥፍራ አናገኝም ።

ይህ ሊሆን የቻለውም ቤተ ክርስቲያን ለላጣት ኑርባት ሳይሆን ራስ ወዳዶች የሆኑ አንዳንድ የቤተ ክርስቲያናት አገልጋይ ነን ባዮች መሆናቸው ግልጽ ነው ቤተ ክርስቲያናችንን የሚጉድዋት በጉያዋ ያሉ ናቸው እንጅ ሌላ ጠላት አለን ብለን አናምንም ። ይህንንም የሚያደርጉበት ምክንያት ከቤተ ክርስቲያን አልፎ ሀገሪቷን ምን ያህል እንደሚጎዱዋት መዛኝ አእምሮና አስተዋይ ጭንቅላት ስለሌላቸው ነው ።

አሁን ግን ይህ የሰበካ ጉባዔ በመቋቋሙና በመጠናከሩ ምእመናኑ የቤተ ክርስቲያን ንዋያተ ቅድሳትን ራሳቸው እንደሚጠብቁ ተስፋችን ሙሉ ነው ምክንያቱም የቤተ ክርስቲያኑ ንዋያተ ቅድሳት በሚገባ እየተመዘገቡ በዘመናዊ አቀማመጥ ማለት ደምበኛ ሳጥናች ተሰርተው በጥብቅ እንዲጠበቁ በመግለጽ ላይ ነን ።

<u>ትንሣኤ</u> ፦ ስለ ትምህርት ቤትስ አያያዝ እንዴት ነው ካህናት እያስተምሩም ፣ መምህራንም ቢሆኑ በሚገባ ወንጌልን አይሰብኩም እየተባለ በከተማ ሆነ በገጠሩ ብዙ ጭሆት ይሰማል ፤ ስለዚህ ወጣቶች ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲቀርቡና ቤተ ክርስቲያናቸውን በበለጠ እንዲያገለግሉ የሸዋ ሀገረ ስብከት ያደረገው ጥረት እንዳለ ቢገልጹልን?

<u>መምህር</u> ፦ በመጀመሪያ ስለ መንፈሳውያን ት ቤቶች ይዞታ እንዴት እንደሆነ ልገለጽ በሸዋ ሀገረ ስብከት በአንዳንድ ቦታዎች መንፈሳውያን ት ቤቶች አሉ ለምሳሌ በየረርና ከረዩ አውራጃ በናዝሬት ከተማ ትልቅ መንፈሳዊ ት ቤት አለ በሶደሬም ተቋቁሟል በመቂ ሀገረ ሕይወትም ት ቤት ተቋቁሟል በወሊሶም እንደ ሌሎቹም ባይመጣጠን በመጠኑ ት ቤት አለ ፣ ይሁን እንጂ እነዚህ ሁሉ በይዞታቸው የሚያስደስቱ አይደሉም ።

በመጀመሪያ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ያዘጋጀቻቸው ትምህርት ቤቶች ሥጋዊና መንፈሳዊ ትምህርት የሚሰጥባቸው ናቸው ግን በእነዚህ አሁን በጠቀስኳቸው ቦታዎች በዘመናዊም ሆነ በመንፈሳዊ በቂ ትምህርት የሚሰጡ የተሟሉ መምህራን ስለሌሉበት የብዙኃኑ ልጆች የሚያረካ ትምህርት ለማግኘት አልቻሉም በዚህም ከፍተኛ ወቀሳ አስከትሎብናል ከዚህ ውስጥ አንድ ያላነሣሁት አለ ይኸውም በደብረ ብርሃን የሚገኘው ከሳቴ ብርሃን ት/ቤት ነው ይህ ት/ቤት ብዙ ሺ ወጭ ሁኖ የተገዛ ሲሆን መሬት ለአራሹ ወይም የከተማ ቤት ለብዙኃኑ ተብሎ ከመታወጁ በፊት ቤተ ክርስቲያን በገንዘቧ በገዛችው መሬት ላይ ት/ቤት ተሠርቶ የዜማና የንባብ ትምህርት ይሰጥበት ነበር አሁን ግን ቤተ ክህ

ወደ ገጽ ፲፩ ዞሯል

---

ህላዌ ለማመን ፈቃደኞች ሆነው ሣለ በሰው ሠራሽ አመለካከት የሚገጥማቸውን የመሥመር ልዩነት ለመጠቆም ያህል ነው ።

ታዲያ በዚህ ሃሳብ ከሚቀርቡት ትንታኔዎች ባጭሩ የሚከተለውን እንመልከት ። እግዚአብሔር በዓለሙ ውስጥ አድሮ (ህልው ሆኖ) ዓለሙን የሚያሠራ አንድ ኃይል ነው ። በዚህ ዓለም ለሚደረገው ለማናቸውም ድርጊት ሁሉ ምክንያቱ እግዚአብሔር ነው ። እንዲያውም ዓለም ራሱ የእግዚአብሔር መገለጫ መልክ ነው ። ዓለምን ሌላ ፣ እግዚአብሔርን ሌላ አድርገን ማየት አንችልም ። እግዚአብሔር ሌላ ፣ ዓለምን ደግሞ ሌላ አድርገን የምናስብ ከሆነ በመካከል ክፍት ቦታ በመተው እግዚአብሔርን ውስጉን በአንድ አካባቢ ብቻ የሚወሰን አድርገን እንዳንመለከተው እንጠንቀቅ የሚል ሲሆን ለዚሁ አባባል አስተዋጽኦ ካደረጉት የጥንት ፈላስፎች መሐል በተለይ ኢራቅሊጦስ የተሰኘው የግሪክ ተወላጅ እግዚአብሔርንና ዓለሙን አንድ በማድረግ ሲናገር እግዚአብሔር ቀንና ሌሊት ነው ፣ እግዚአብሔር ክረምትና በጋ ነው ። እግዚአብሔር ጦርነትና ሰላም ፣ ረሃብና ጥጋብ ወዘተ ነው እያለ ያስተምር እንደነበር ተጽፎአል ።

ለዚህም አባባል በዶ/ር የማነ ገብረ ማርያም የፍልስፍና ትምህርት መጽሐፍ የተሰጠው መልስ እንዲህ የሚል ነው ። "እግዚአብሔርን ከዓለሙ ጋር አንድ አድርገን ካሰብነውና ከዓለሙ የተለየ ወይም ውጭ የሆነ አድርገን ካልተመለከትነው በቀር ቁጥራችን ከኢአማንያን የራቀ ነው ማለት አያስደፍርም ። የሃይማኖት ዋና መሠረቱ እግዚአብሔር ከዓለሙ የተለየ ሆኖ ከዓለም በፊት እንደነበረና ዓለምም በርሱ እንደተፈጠረ ማመንና መቀበል ነው ። ይኸውም እግዚአብሔር ሲባል በሙሉ ዓለሙን የሚጠቅስ ከሆነ ሰውም ሁሉ የዚሁ የእግዚአብሔር አንዱ ክፍል መሆን ነውና ከእኛ ከሁላችን የተለየ ከዓለም ውጭ የሆነ አንድ ኃይል መኖሩን ከመካድ ያደርሳልና ወደ ማን ይቀርባል?

ደግሞ አንድ ነገር ሁሉን ሊሆን አይችልም ። ማለት ብርሃንም ጨለማም ፤ ሰማይም ምድርም ደግሞ ክፉም ቀንም ሌሊትም ሊሆን ከቶ አይችልም ። እርግጥ እግዚአብሔር በዓለም ሁሉ ምሉእ ነው ፣ እርሱ የሌለበት ሥፍራ የለም ብለን እናምናለን ። ይህ ማለት ግን እግዚአብሔር መላውን ዓለም ነው ማለት አይደለም ። እግዚአብሔር መንፈስ ስለሆነ ዘመንና ሥፍራ አይወሥኑትም ማለት ነው እንጂ ለዚህም ማስረጃችን በዮሐንስ ወንጌል 4 ቁጥር 20 - 24 በግልጥ ተጽፎአል ።

ስለዚህም የሐዋርያ ጳውሎስን መልእክት በመደገፍ ማለት የሚገባን የትክክለኛ ሃይማኖት መግለጫ ይህ ነው ። "ሃይማኖት ማለት ተስፋ በተደረገው ነገር ማመን ነው ። የማይታየውንም ነገር እንደሚታይ አድርጎ መቀበል ነው ። ዓለማት በእግዚአብሔር ቃል እንደተፈጠሩ የሚታየውም ነገር ሁሉ ከማይታየው መሆኑን በመግለጥ ለአበው (ለሽማግሎች) እንደተመሰከረላቸው እናውቃለን ። የተባለውን ማስረጃ በዕብ. 11. 1 - 3 መመልከት ይቻላልና በፓንቴይዝም ፍልስፍናዊ ሒደት የተተነተነው ሰው ሠራሽ የሐ ብ መሥመር ልዩነት ለሃይማኖታችን ዕንቅፋት ሊሆንብን እንደማይችል መታወቅ አለበት ።

ቄስ መክብብ አጥናው





www.ethiopianorthodox.org

# ምን እንርዳዎ ?

ይህ ዓምድ አንባቢዎች ችግራቸውን የሚገልጹበት ፣ ለችግራቸው መፍትሔ የሚሰጡበት ፣ ጥያቄና መልስ የሚያቀርቡበት ስለሆነ ምን እንርዳዎ ተብሎ ተሰይሟል ።



አዘጋጅ ተስፋ ጥሩነህ
ስልክ ቍጥር 11-66-16
የፖ.ሣ.ቁ. 31-37
አዲስ አበባ

ሚስቴ ቃሌን አትሰማም ፣ አታክብረኝም ፣ ትንቀኛለች ፣ በሰው ፊትም ታዋርደኛለች ይህ የወንዶች አቤቱታ ነው ።

«ባሌ የራሱ መብት እንዲጠበቅለት ሁልጊዜ ይጥራል ነገር ግን የእኔን መብት አይጠብቅልኝም ፣ እየሰከረ ይደበድበኛል ያለ ሰዓት እየገባ ጤና ይነሣኛል» ይህ ደግሞ የሴቶች ሁሉ እንጉርጉሮ ነው ፣ ስለዚህ የምንሰጠው ምክር እንደሚከተለው ይሆናል ።

"በአንተ ላይ ሊደርስብህ የማትፈልገውን ነገር ሁሉ በሌሎች ላይ እንዲደርስ አታድርግ" የሚል የወርቃማው ሕግ ክፋሌ አለ ። ይህም ክርስቲያናዊ መመሪያ ማንም ሰው የሌላውን የተፈጥሮ ጓደኛውን መብት እንዳይዳፈር ማገጃ ሕግ ሆኖ የኖረ መሆኑ ታሪካዊ ሐቅ ነው ።

በተለይም የኑሮ ጓደኛ መብት ማለትም ባል የሚስቱን ፣ ሚስትም ደግሞ የባልዋን መብት መጠበቅ እንደሚገባቸው ከዚህ ወርቃማ ሕግ ሊማሩት የሚገባ ቁምነገር አለ ። በዕርግጥም በአንዳንድ ባልና ሚስት መካከል ይህ ሕግ ዋልታና ምሰሶ ሆኖ ፍቅርንና ሰላምን አጽንተው ለቤተሰባቸው ጥሩ ምሳሌነትን በማሳየት በመልካም ጭዋነትና ሥነ ሥርዓትን በተሞላ መግባባት ተጣብቀው እንዲኖሩ አድርጎአል ። በበዚህም ወርቃማ ሕግ በቢሊዮን የሚቆጠሩ የዓለም ኅብረተሰቦች ተባርከውበታል ለማለት የሚያስደፍረን በቂ ምክንያት አለ ።

ነገር ግን በአንጻሩ ከዚህ ወርቃማ ሕግ ውጭ በራሳቸው ፍላጎት የሚመሩ ግለሰቦች የኑሮ ጓደኞቻቸውን መብት በመድፈር ማለትም አንዳንድ ባሎች አልፈው ተርፈው ሚስቶቻቸውን እንደ ሕፃን አፍሺን ያዥ በማለት እጅ ከወርች አሥረው የሚገርፉ (የሚቀጡ) በቁጣና ግልምጫ እያሸቆጠቆጡ ሥልጣናቸውን ለማሳየት በቤተሰባቸው ላይ ነግሠው በትዕቢት የናጠጡ የቀድሞው ሥርዓት ርዝራዦች አሁንም እንዳሉ ይነገራል ። ያለጥርጥር የወንድን የበላይነትና አጉል ጀብደኛነት የሚያንጸባርቁ ብዙ ርካሽ ምልክቶች አሉ ።

በተለይም በሀገር ቤቱ ኅብረተሰብ መካከል የባልና ሚስት እኩልነት እንዲሰፍን በባልና ሚስት መካከል መተሳሰብና የሥራ መደጋገፍም ባህል እንዲለመድና ይህ የሴት ፣ ያ የወንድ ሥራ ነው ተብሎ ሳይለይ ሁሉም ለሁሉ አስፈላጊ የመሆኑን ያህል ተባብሮ የመሥራት ዝንባሌ እንዲኖር ለማድረግ ከፍተኛ የትምህርት ዘመቻ ማስፈለጉ ገሐድ እየሆነ በመከሠት ላይ ነው ። በሀገር ቤት እንደባህል ሆኖ ሚስቱን የማይደበደብ ወንድ ወይም ባልዋ የማይቀጣት ሴት ቢኖሩ በጣት የሚቆጠሩ በጣም ጥቂቶች ብቻ መሆን አለባቸው ። በተለይ ወንዱ ትዕግሥተኛና ጭምት ከሆነ የወንድ አልጫ ሴታሴት ወዘተ ተብሎ እስከመሰደብ ይደርሳል ።

ይህን ለማካካስ በነጋ በጠባ ዱላ ማንሣት በኡኡታ ሠፈር ማሸበርበቀድሞው ሥርዓት የተለመደ እንደነበር ግልጥ ነው ። ምንም እንኳ ከለውጡ ወዲህ በመጠኑ የመሻሻል ምልክት ቢያሳይም በአንዳንድ ሴቶች ላይ ባሎች የሚፈጽሙት ዕብሪት ገና ሥርነቀል ለውጥ ስላልተደረገበት ብዙ አትኩሮት ሊደረግበት ይገባል እንላለን ። በአንፃሩም አንዳንድ ሴቶች (አልፎ አልፎ) የባሎቻቸውን መብት በመዳፈር በአደባባይ መሳደብና የውስጥ ገመናቸውን አጋልጠው ሲነታረኩ መስማት ከጥንቱ ሥርዓተ ኑሮ የወረሥነው ምን ዓይነት ርካሽ ባህል እንዳለ የሚያሳይ ነው ።

አዎ ምላሳቸው እንደ አንደርቢ ሆኖ የነገር እሳት በመትፋት የኑሮ ጓደኞቻቸውን ማስከፋትና ማሳዘን እንደአርበኛነት ሙያ የሚቆጠር መስሎ የሚታያቸው ብዙ ጀብደኞች ሴቶች አሉ ። አንድ ጊዜ አንድ ሰው ሚስቱ በማድቤት ምጣድ አስምታ ስትጋግር በድንገት መጥቶ ባልታወቀ ጥፋት ሲደበድባት ተበሳጭታ በእጇዋ የያዘችውን የሊጥ ማዞሪያ ጣሳ ብትወረውር እትከሻው ላይ ስታነጣጥርበት ከራስ ጠጉሩ እስከ እግር ጥፍሩ ኮቱና ሱሪው ተበክሎ ስለነበር የጎረቤት ሰዎች ለግልግል ደርሰው ሊጡን እንጥረግልህ ቢሉት "ተውት እባካችሁ ጉድዋን ሰው ይይላት" አለ ይባላል ። ታዲያ ጉዱ የርስዋ ብቻ ነበርን ? እርሱስ የኑሮ ጓደኛው አካሉ የሆነችውን ሚስቱን የእሳት ወላፈን እየገረፋት በምትጋግርበት ማድቤት ገብቶ መደብደብ ጉደኛነት አይደለምን ?

ሌላው ደግሞ ከሚስቱ ጋር ሠርግ ቤት ተጠርቶ ሔዶ ሲበሉ ሲጠጡ ውለው

ወደ ገጽ ፲፩ ዞሯል



# የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ዜና

አዲስ አበባ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅት ክርስቲያናውያን መጽሔቶችንና ጋዜጦችን በአሥራ አራቱ የኢትዮጵያ ሀ/ስብከቶች ለማዳረስ ባለፈው የታህሣሥ ወር 1971 ዓ.ም. ባደረገው የመጀመሪያ ሙከራ የሚከተለው ውጤት ተገኝቷል ።

ወለጋ ፡- በወለጋ ሀ ስብከት በነቀምቴ ከተማ የሚገኙ የቤተ ክህነት ኃላፊዎችና የሰበካ ጉባኤ አባላት በየአሥራ አምስቱ ቀን ከሚታተመው ድምፀ ተዋሕዶ ጋዜጣ 500 ፣ በየወሩ ከሚታተመው ትንሣኤ መጽሔት 100 በመውሰድ ደንበኞች ለመሆን ተመዝግበዋል ።

ግምቢ፡- በግምቢ አውራጃ ያሉ የቤተ ክህነት ኃላፊዎችና የሰበካ ጉባኤ አባላት 400 ጋዜጣ ፣ 100 መጽሔት ለመውሰድ ፈቅደዋል ።

ጎጃም፡- የባሕርዳር የክብረ ተዋሕዶ ወጣት ማኅበር 500 ጋዜጣ ፤ 200 መጽሔት ፤

ዳንግላ፡- የዳንግላ አውራጃ ቤተ ክህነት 100 ጋዜጣና 50 መጽሔት ፤

ደብረ ማርቆስ፡- በደብረ ማርቆስ የሚገኘው የሃይማኖተ አበው ማኅበር 100 ጋዜጣና 50 መጽሔት ፤

ጨሞጋ፡- በጨሞጋ ወረዳ የተቋቋመው የፈለገ ዐርዝ መንፈሳዊ ት/ቤት 100 ጋዜጣና 50 መጽሔት ፤

ብቸና፡- የብቸና አውራጃ ቤተ ክህነት 50 ጋዜጣ 25 መጽሔት ፤

ሞጣ፡- የሞጣ ቤተ ክህነት 50 መጽሔት 100 ጋዜጣ ለመውሰድ ፈቃደኞች ሆነዋል ፤

ኤሉባቦር፡- የኤሉባቦር ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት በየወሩ 100 መጽሔትና 200 ጋዜጣ እየተቀበለ ለአካባቢው ክርስቲያን አንባቢዎች ለማዳረስ የፈቀደ መሆኑ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅት መልእክተኞች ባገኙት የጥናት ሙከራ መሠረት ተገልጧል ።

***

ሩሲያ፡- በተባበሩት ሶቭዬት ሶሻሊስት ሪፐብሊክ ላለው የአብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ከ1940 ዓ.ም. ወዲህ የኤሮጳ አህጉር የተባበሩት ከመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር 25000 በሩስያ ቋንቋ የታተመ መጽሐፍ ቅዱስና 2000 የመ/ቅ ቃላት መፍቻ እንዲገባለት መንግሥት ፈቀደ ።

የሩስያ መጥምቃዊት ቤተ ክርስቲያን ባለፉት ዓመታት 10000 መ/ቅ በሩስያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ማተሚያ ቤት ያሳተመቻቸው በማለቁ ፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን ፈላጊ ቁጥር በጣም እየበዛ በመሄድ ላይ መሆኑን የተባበሩት የዓለም መ ቅ ማኅበር በቁጥር 104 ሕዳር ወር እትሙ ገለጸ ።

***

ኬንያ፡- በምሥራቅ አፍሪካ የሚገኙ የፕሪስቤተሪያን ቤተ ክርስቲያን የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ሕዳር 22 ቀን 1971 ዓ.ም. በናይሮቢ ከተማ ተሰብስቦ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ የተራድኦ ድርጅት 17425 የኢ.ት.ብር ለስዋፖ ነፃ አውጪ ድርጅት የሰጠውን ርዳታ ደግፈዋል ። ቤተ ክርስቲያን ለነፃነታቸው የሚዋጉትን ትደግፋለች ፣ በነፃነት እጦት ምክንያት የማኅበራዊ ኑሮ አቸው የተጉሳቆለባቸውን በመሀይምነት የተጠመዱትን መርዳት ዓላማዋ ነው ካሉ በኋላ አንዳንድ የኤሮጳ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች በስጦታው ቅር ከተሰኙ እነርሱም ነፃ እንውጣ እያሉ የሚታገሉትን የአርበኞች ጥያቄ ለማፈን የሚሞክሩትን መንግሥታት በመጀመሪያው ምክር ይስጧቸው በማለት አሳባቸውን ደምድመዋል ። በማለት ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ተገለጸ ።

***

ጀርመን ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ፡- በምሥራቅ ጀርመን የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ከ1-6 ሚሊዮን የጀርመን ገንዘብ ለክርስቲያናዊ ልማት ነክ እንቅስቃሴዎችና ለስደተኞች መርጃ የሚሆን ርዳታ ለዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ለመስጠት የተዘጋጁ መሆናቸው ከበርሊን ተገለጸ ።

እነዚህም አብያተ ክርስቲያናት ለሩማንያ ፣ ለአንጐላ ፣ ለሁንጋርያና ለፖላንድ መንፈሳውያን ተቋሞች 1507550 የጀርመን ማርክ ረድተዋል። በተጨማሪም በናዚ ጦርነት ለአለቁትና ለተጐዱት 13 ሚሊዮን ሕፃናት መታሰቢያ እንዲሆን በቅርቡ በዋርሶ ከተማ ለተሠራው የሕፃናት ክሊኒክ 90000 የጀርመን ማርክ ረድተዋል ሲል የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ኢኩሜኒካል ፕሬስ በታኅሣሥ ወር እትሙ በቁጥር 33/45 ገለጸ ።

***

ሩማንያ፡- ቡካሬስት ከተማ የሚገኘው የሩማንያ ኦርቶዶክስ ማተሚያ ቤት የተቋቋመበትን 300ኛ ዓመት ባለፈው ታህሣሥ ወር አክብሯል ። ማተሚያ ቤቱ የተቋቋመው በታህሣሥ ወር 1678 ዓ.ም. ነበር ። ይህ ማተሚያ ቤት የመጀመሪያውን መጽሐፍ ቅዱስ በሩማንያ ቋንቋ አትሞአል ፣ ለቤተ ክርስቲያኒቱና ለምእመናን የሚያገለግሉ ልዩ ልዩ መጻሕፍትን እያሳተመ ያወጣል ። ከ1964 ዓ.ም. ጀምሮ 200000 ቅጅ መጽሐፍ ቅዱስ አትሞአል ለእትመቱ ወረቀቱን የለገሰው የተባበሩት የዓለም የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ነው ።

የሩማንያ ኦርቶዶክስ ፓትርያርክ ብፁዕ አቡነ ጁስቲን ለተባበሩት የዓለም መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር አባሎች በብዙ ሺህ የሚቆጠር መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስፈልጋቸው ገለጹላቸው ሲል ቁጥር 105 የታህሣሥ ወር የማኅበሩ መጽሔት ገለጸ ።

***

ሕንድ፡- የሕንድ አብያተ ክርስቲያናት በልማት በኩል ለመሰለፍ ባለፈው ሕዳር 86 አባላት ያሉበት ስብሰባ በኩልኩታ ከተማ ተካሂዷል ። ውይይቱን ያዘጋጀው የቅዱስ ሲኖዶስ የማኅበራዊ ጉዳይ አገልግሎት ክፍል ነበር ።

ውይይቱ ያተኮረው ቤተ ክርስቲያን ከመንግሥት ጋር ተባብራ በልማት ሥራ ለመሳተፍና ችግረኞች ራሳቸውን በራሳቸው እንዲረዱ ንቃተ ኅሊና ለመስጠትና ለማስተማር እንድትችል መንገድ ለመፈለግና ኅብረተሰቡም በኢኮኖሚ ፣ በፖለቲካ ፣ በባህልና በሃይማኖት በማኅበራዊ ኑሮ ተሳ

ወደ ገጽ ፲፩ ዞሮአል



www.ethiopianorthodox.org

# ሐዋርያት ለተረሱ ሕዝቦች

ካለፈው የሚቀጥል

ባለፈው ጽሑፍ የተረሱ ሕዝቦችን ለማገልገልና እየተዘዋወረ ለማስተማር የመጣው እውነተኛ ሊቀ ካህናት ክርስቶስ ለሐዋርያትና ለካህናት በጠቅላላው ለወንጌል መልእክተኞች ሁሉ መመሪያ እንደሰጠ ከገለጽኩ በኋላ መጥምቁ ዮሐንስም ከገጠር ወደ ከተማ የተረሱ ሕዝቦችን እንዴት እያስተማረ እንደመጣ አብራርቼ ነበር ።

አሁን ደግሞ ለሐዋርያትና ለተረሱ ሕዝቦች ትርጉማቸውን መስጠት አስፈላጊ ሆኖ አግኝቸዋለሁ ። ሐዋርያት ማለት ከሁሉ በፊት ለሥጋዊው ሕይወት ማቋቋሚያ የሚሆን በገዛ ወዙ ሠርቶ ዳቦ ማግኘት የሚያሻ መሆኑንና የሕሊና ንቃት ፣ የመንፈስ እንቅስቃሴ በወንጌል ትምህርት የሚገኝ መሆኑን ለማስተማር ወደ ተረሱ ነኩት አይወዱም በጸሎትም እርዝመት እያመካኙ ከመበለቶች ቤት ሳይቀር እየገቡ ከመብላታቸው ሌላ አዝሙድ ፣ እንስላል ፣ ከሙን ሳይቀር አሥራትና በኩራት እየተቀበሉ ሲወስዱ ፍርድንና ምሕረትን የሕሊናም ሆነ የመንፈስ ንቃት ለተረሱ ሕዝቦች ሳይሰጡ በከተማ ቁጭ ብለው የራሳቸውን ኑሮ ብቻ ያሻሽሉ እንደነበር ታላቁ መጽሐፍ ይነግረናል ።

በጣም የሚያሳዝነው ደግሞ በገጠር የሚኖሩት የተረሱ ሕዝቦች የተከሉትን የወይን ፍሬ አርሰው ያመረቱትን እህል የሠሯቸውን የሸክላ ዕቃዎች ለመሸጥ ወደ ከተማ ሲያመጡ ከገዙ በኋላ ወደ ቤታቸው ሄደው ከረከሱና ከተናቁ ሕዝቦች የገዛነው ዕቃ ስለሆነ እኛን ስለሚያረክሰን እያሉ እጃቸውን ሆነ ዕቃቸውን ያጥቡ



ተረስተው የነበሩ ወገኖቻችን

ሕዝቦች የሚሄዱ እራሳቸውን ሳይሆን ሌላውን የሚያገለግሉ ሌላውን የሚጠሉና የሚንቁ ሳይሆን እራሳቸውን የሚንቁና የሚጠሉ የወንጌል መልክተኞች ማለት ነው ።

የተረሱ ሕዝቦችም ማለት ተፈጥሮ ያደላቸውን ከፀሐይ ብርሃን ፣ ከአየርና ከውሃ በቀር እንደ ሕክምና እንደ ትምህርት እንደ ሥልጣኔና እንደ ንቃተ ሕሊና በጠቅላላ ሀገሪቱ ከምትሰጠው በረከት የማይካፈሉና ቤተክርስቲያንም የምትሰጠውን የወንጌል ትምህርት የማይሳተፉ ማለት ነው ።

ይህንንም ለመረዳት ብንፈልግ በሙሴ ወንበር ተቀምጠው የነበሩት ጸሐፍትና ፈሪሳውያን ከባድና አስቸጋሪ ሸክም ተብትበው በሰው ትከሻ ይጭናሉ እነርሱ ግን በጣታቸው እንኳ ሊነበር እንዲያውም ለተከታዮቻቸው በሚሰጡት ትምህርት እንዲህ ካሉ ሰዎች ጋር የተነጋገረና ከቤታቸው ሔዶ ያደረ አብሮ የበላና የጠጣ ሁሉ የረከሰ ነው እያሉ ያስተምሩ ነበር ይህም እነጋገር በእነርሱና በተረሱ ሕዝቦች መካከል ክርስቶስ ሰው ሆኖ ወደዚህ ዓለም እስከመጣ ድረስ ታላቅ ገደል ሆኖ ለያይቶአቸው ይኖር ነበር ።

ክርስቶስ ከመጣ ወዲህ ግን በያዕቆብ ምንጭ አጠገብ ቁጭ ብሎ ተንቃ ትኖር የነበረችውን የሰማርያን ሴት ሕይወቷን በመንፈስ ለውጦላታል ። በእርሷም አማካይነት ሄዶ በመንደሩዋ ይኖሩ የነበሩትን የተረሱትን ሕዝቦች አስተምሮ አዲስ ሕይወት ሰጥቶአቸዋል ። በተጨማሪም ወደ ጢሮስና ወደ ሲዶና ሲያልፍ ተረስታ የነበረችውን የአንዲት የከንአናዊት ሴት ልጅ ከበሽታዋ ፈውሶአታል ። በጠቅላላው በመንፈስ የተረሱትን ብቻ ሳይሆን በሥራ የተረሱትንም ጭምር እንጀራ አበርክቶ አጥግቦአቸዋል የታመሙትንም ፈውሶአቸዋል ።

ደቀ መዛሙርቱም ቢሆኑ የኢየሩሳሌም ኤጲስ ቆጶስ ከነበረው ከያዕቆብ በቀር ዓለምን ዕጣ በዕጣ ተከፋፍለው ሄደው የተረሱትን ሕዝቦች የሕሊና ንቃትና የወንጌልን ትምህርት እየሰጡ ወደ ሥራ ዓለም እንዲሠማሩ አድርገዋቸዋል ።

እንግዲህ ወደ ሀገራችን መለስ እንበልና ሐዋርያትና የወንጌል መምህራን ለተረሱ ሕዝቦች ምን ዓይነት አገልግሎት አበርክተዋል የሚለውን እስቲ እንመርምር ። ከ4ኛው መቶ ዓመት እስከ 19ኛው መቶ ዓመት የነበሩት የሀገራችን ሐዋርያትና ካህናት በመሐል አገርና በከተማ ብቻ ሳይሆን በገጠሪቱ ኢትዮጵያና በየጠረፉ እየተዘዋወሩ የሕሊና ንቃትና የመንፈስ እንቅስቃሴ ለተረሱት ሕዝቦች ሰጥተዋል የወንጌልንም ብርሃን አብርተዋል ። ለዚህም ምስክር የሚሆነን በየገጠሩና በየጠረፉ የተተከሉት አብያተ ክርስቲያናትና ያገለግሉ የነበሩት ካህናት ምስክሮች ናቸው ።

ፋሺስት ኢጣልያ ድል ሆኖ ከወጣ ወዲህ ግን ያሉት የዘመናችን ሐዋርያትና የወንጌል መምህራን በገጠሪቷ ኢትዮጵያ ማስተማራቸውን እየተውና ሞፈር ቀንበራቸውን እየሰቀሉ የግል ሀብት ለመሰብሰብና የራሳቸውን ምቾት ለማሳመር ሹመት ለመፈለግ አዲስ አበባ ከተማ ገብተው በብዛት ተሰገሰጉ በገጠሪቷ ኢትዮጵያና በየጠረፉ ያሉት የተረሱት ሕዝቦች ለዘመናት የተሸከሙትን የችግር ቀንበር ሰብሮ ከረሃብ ፣ ከበሽታ ፣ ከመሐይምነት ከእርዛት ፣ ከሥራ እጦት የሚያላቅቃቸው አጥተው ሲጮሁ አንድም ሐዋርያ የችግራቸው ተካፋይ ሆኖ አልተገኘም እያንዳንዱም ሐዋርያ ሐላፊነትና መንፈሳዊ ግዴታ ሲኖርበት ግዴታውን አልፈጸመም ።

መጽሐፈ መክብብ ምዕራፍ 4 ከቁጥር 1-2 በተረሱት ሕዝቦች ላይ ይፈጸም የነበረውን ግፍ ሲናገር ‘‘ከፀሐይ በታችም የሚደረገውን ግፍ ሁሉ አየሁ እነሆም የተገፉት ሰዎች እንባ ነበረ የሚያጽናናቸውም አልነበረም’’ ብሏል ። እርግጥም ከለውጡ በፊት በነበረው ሥጋዊውም ሆነ መንፈሳዊው አስተዳደር ጥቂት መንፈሳውያን መሪዎችና የወንጌል መምህራን ከጥቂቶች ካህናት ተለይተው ሁሉ የኔ የሚለው የስግብግብነት ጠባይ ስላጠቃቸው የድሆች ካህናትና የተረሱ ሕዝቦች እንባ እንደ ክረምት ጐርፍ ሲፈስ ውሃ የፈሰሰ የማይመስላቸው ችግረኞችም ተርበው ሲያለቅሱ ሲጮሁ የውሻ ቡችላ እንደ ጮኸ የማይቆጥሩ መሆናቸው የታሪክ ሐቅ ነው ።

ለምሳሌ በቀድሞ ዘመን ለአሠሪነትና ለአስተዳዳሪነት የሚመረጡት ሐዋርያት በእኩልነት የሚያምኑ ፣ ርህራሄ ያላቸው ፣ የተረሡትን ሕዝቦች እየዞሩ የሚጐበኙ ሠርተው የሚያሠሩ ለኔ ከማለት ይልቅ ለኛ የሚሉ ነበሩ ።

በዘመናችን ያሉ አንዳንድ ሐዋርያት ግን በገንዘብ ፍቅር ስለተያዙና ለግል ጥቅም ተገዥ ስለሆኑ የተረሱትን ሕዝቦች ሄደው ከማገልገል ይልቅ እራሳቸውን ማገልገል ወደዱ ።

አንድ ሊቅ እንደ እነዚህ ስላሉት ሰዎች ሲናገር ከሰዎች ሁሉ የማይታዘንለት የመጨረሻ ዕድለ ቢስ ፍጡር የሌሎቹን ጠቃሚ ምክርና ተግሣጽ ሳይቀበል በራሱ ሐሳብ ብቻ የሚመራ ነው ። እንዲህ ያለውም ሰው ዐይኑን በግል ጥቅም ጋርዶ ወደ ጥፋት ከመገስገስ አያቋርጥም በውድቀቱ የሚራራለት የለም’’ ብሏል ።

እርግጥም በጣም ያሳዝናል ምክንያቱም በአካባቢው በጐረቤቱ ብዙ ሰው እያለ ከሰው ጋር መኖር ከሰው ጋር መመካከር ጠልቶ ብቻውን ስለሚኖር ነው ።

ይህ እንዳይሆን ቤተክርስቲያን የለውጡን ፈር ተከትላ ሠርተው የሚያሠሩ ነቅተው የሚያነቁ ለእኩልነት የሚያምኑ ማቁን ጨርቁን ሳይሉ ወደ ተረሱት ሕዝቦች የሚሄዱ እውነተኞች ሐዋርያትን በመብራት መፈለግ አለባት ።

አንድ የኅብረተሰብአዊነት ፍልስፍና መሪ ለተረሱ ሕዝቦችና ለጭቁን ገበሬዎች ንግግር በሚያደርግበት ጊዜ እነርሱ ያደፈና ድሪቶ ለብሰው ስለነበር እርሱ ግን ከነርሱ ለየት ያለ አዲስ ልብስ ለብሶ ነበር ከዚህም የተነሣ በማንኛውም ነገር እኛን መምሰል ወደ እኛም መምጣት አለብህ አሉት እርሱም እናንተን ወደ እኔ ለመሳብ እንጂ እናንተ እንድትስቡኝና ወደ እናንተ እንድመጣ አይደለም አላቸው ይባላል ። እንዳለውም ወደ ተረሱት ሕዝቦች የሚላኩት ሐዋርያት እነርሱ ወዳሉበት ድህነትና ችግር መሳብ ሳይሆን የተረሱትን ሕዝቦት በሥራ ብልጽግና እንዲሳቡና ወደ እድገት ደረጃ እንዲደርሱ በንቃተ ሕሊና በመንፈስ እንቅስቃሴ ወደ እነርሱ መሳብ እንጂ እነርሱ ወደ እነዚያ መሳብ የለባቸውም የማንቃትም የመሥራትም አላማው ይህ ነውና ።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ

# ስለ ሸዋ ሀገረ ...

ከገጽ ፯ የዞረ

ነቱ መርሐ ግብር የሌለው ከመሆኑ የተነሣ የከተማው ማዘጋጃ ቤት የነበረውን ቤት አፍርሶ ድንጋውንና ቆርቆሮውን ሁሉ ስለ ወሰደው ልጆቻችን ተበትነዋል ትምህርታቸውን አቋርጠዋል የሚል አቤቱታ ቀርቦልናል ይህንን መሠረት አድርገን ለቤተ ክህነቱም ብንጽፍ መልስ አላገኘንበትም ።

ስለዚህ በሀገረ ስብከታችን ያሉት ጥንታውያን ት/ቤቶችም ሆኑ ዘመናውያን ት/ቤቶች ቁልቁል እየወረዱ ነው የሚታዩት በዚህም ሁናቴ ጽኑ ሐዘን ይሰማናል ስለ ሀገራቸውና ስለ ቤተ ክርስቲያናቸውም ተቆርቁረው ደመወዝ እያገኙ መስዋዕት ለመሆን የተዘጋጁ ፈቃደኞች መምህራን አልተገኙም ቢገኙም በመጠኑ ነው ስለዚህ ከባድ ችግር ገጥሞናል በማለት መምህር ሰሎሞን ገብረ ሥላሴ በሰፊው ገልጠውልናል ።

# የዓለም አብያተ ...

ከገጽ ፱ የዞረ

ትፎ የሚያገኝበትን መንገድ ሁሉ ተወያይቶ ቤተ ክርስቲያንም ድርሻዋን ለማበርከት የምትችልበትን መንገድ ውይይቱ ቀይሶአል ሲል የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ኢኩሙኒካል ፕሬስ በ32 45ኛው እትሙ ገልጿል ።

***

ጋና፡- በጋና የምትገኘው የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ጽ/ቤት እንግሊዘኛ ለሚናገሩ የምዕራብ አፍሪካ አገሮች ለናይጀሪያ ፣ ለጋና ፣ ለላይበሪያ ፣ ለሴራሊዮንና ለጋምቢያ የቤተ ክርስቲያን የመገናኛ ማደራጃና ማሠራጫ ሠራተኞች ስለክርስቲያናዊ አሠራርና ሰዎችን በሁለንተና ባለሙያዎች ለአገልሎት ማዘጋጀት ከሚያዝያ 9-13 ቀን 1971 ዓ.ም. ትምህርታዊ ሴሚናር የሚሰጥ መሆኑን የዓለም ክርስቲያናዊ የመገናኛ ማደራጃና ማሠራጫ ማኅበር ጋዜጣ በ3ኛው ቁጥሩ ገለጸ ።

***

### አፍሪቃውያን ሠዓሊዎች መጽሐፍ ቅዱስን ያጠናሉ፤

ናይሮቢ፡- ከስድስት የአፍሪቃ ሀገሮች የተወጣጡ ክርስቲያኖች ተካፋዮች የሆኑበት የመጽሐፍ ቅዱስ የጥናት ቤተ ተማባር ከመስከረም 21 እስከ ጥቅምት 4 ቀን 1971 ዓ.ም. ለመጀመሪያ ጊዜ በናይሮቢ ተከፍቶ ነበር ። በጥናቱ ላይ ሁለት አፍሪቃውያን ሠዓሊዎች ተገኝተዋል ። እነርሱም ኢትዮጵያዊው ሠዓሊ ገብረ ክርስቶስ ደስታና ታንዛንያዊው ሠዓሊ ዮሐንስ ሊሞ ነበሩ ። የጥናቱ ዓላማ መጽሐፍ ቅዱስን ለአፍሪቃውያን በሚስማማና በሚረዳ ሁኔታ ለመተርጐም ነው ለምሳሌ ወርቅማና ረዥም ሆኖ የተገለጠው የክርስቶስ ጠጉር ፣ እንደዚሁም ቀይ የሆነው መልኩ ለአውሮፓዊ እንጂ ለአፍሪቃዊ አይረዳም ፣ ስለዚህ ይህንና ይህን የመሰለውን ሁሉ ለማረም የጥናቱ ጓድ ያሰበበት መሆኑን ወርልድ አሶስዬሽን ፎር ክርስቲያን ኮሙኒኬሽን የተባለው ጋዜጣ በታህሣሥ ወር 1971 ባወጣው በ35ኛው እትሙ ገለጠ ።

# ምን እንርዳዎ ?

ከገጽ ፰ የዞረ

ሲመለሱ ይሰክርና ሚስቱን መደብደብ ይጀምራል ፣ እርሱ በስካር ብዛት ዝሎ (ተዳክሞ) ሳለ ሚስቱ ግን ብዙ ስላልጠጣች የኃይልዋ ሚዛን አልተዛባም ነበርና በትሩ ሲበዛባት አፀፋውን ለመስጠት በመገደድ ድንጋይ አንስታ በግምባሩ ላይ ትመርግበታለች ። ስካር አደንዝዞት ስለነበር ለጊዜው በትሩ ባይሠማውም ግምባሩን ቢዳብስ በደም ተነክሮ ስላገኘው ‘‘ኸረ ጉድ ነው የግንቦት ልደታ ምኑን አመጣሽው’’ አለ ይባላል ።

እንግዲህ የአንዳንድ ባልና ሚስት ሕይወት በዚህ ዓይነት ሁኔታ ላይ ይታያል ። የምንፈልገውም የዚህ ጽሑፍ ዋና መልእክት ባል የሚስቱን ሚስትም የባልዋን መብት መድፈርትተው ሁለቱም በእኩልነት ደረጃ ተሳስበው እንዲኖሩ ማሳሰብ ነው ። አበውም ሲተረጉሙ ‘‘እግዚአብሔር ሴትን ከወንድ ራስ አጥንት አንሥቶ አልፈጠራትም ፣ ይኸውም በመብት ከወንድ በላይ እንድትሆን አልፈለገም ወይም ከእግሩ አጥንቶች አንሥቶ አልፈጠራትም ፣ ምክንያቱም ሴት ከወንድ በታች እንዳትሆንና መብትዋ እንዲረገጥ አልፈለገም ። ነገር ግን ሁለቱም በእኩልነት ተባብረውና ተደጋግፈው እንዲኖሩ ፈቅዶ ከጐኑ አጥንቶች አንሥቶ ፈጠራት ። ደግሞም በልቡ አጠገብ ከምትገኝ አጥንት አንሥቶ ፈጠራት ። ይኸውም የተወደደች እንድትሆን ፈቅ





www.ethiopianorthodox.org

# ሃይማኖት ያለ ምግባር አልጫ ነው

በመጀመሪያ ሃይማኖት ምንድነው ? የሚል ጥያቄ በአእምሮአችን ሊኖር ይችላል ለዚህም መልስ ሐዋርያው ቅ ጳውሎስ ወደ ዕብራውያን በጻፈው መል እክቱ ሲያብራራ "ሃይማኖት ማለት ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያረጋግጥ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው" ብሏል ዕብ. ም.11 ቁ 1 እንደዚሁም የቤተ ክርስቲያናችን ሊቅ የሆነው ዮሐንስ አፈወርቅ ስለዚሁ ጉዳይ ሲጽፍ ሃይማኖት መሠረት ናት ሌሎቹ ግን ግድግዳና ጣሪያ ናቸው ሲል አትቷል ።

እዚህ ላይ የሁለቱንም ሰዎች ሃሳብ አጣምረን የተመለከትን እንደሆን የሁለቱም አንድ እንጂ ምንም ልዩነት የለውም ስለዚህም ሁለቱም አንድ ናቸው ማለት ነው ። እንዲህ ከሆነ ዘንድ ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያረጋግጥልን ሃይማኖት በሥራ ሲተረጐም ነው ።

እንደዚሁም ምግባር ማለት ደግሞ ሥራ ማለት ሲሆን ሃይማኖት የሚያዘ ውን መልካም ሥራ ሁሉ በተግባር መግ ለጽ ማለት ነው ። እንግዲህ ስለ ሃይማ ኖትና ምግባር ከተነጋገርን አሁን ደግ ሞ አልጫ ማለት ምን ማለት እንደሆነ እንመልከት ይህ ቃል ሁለት ትርጉም ያለው ይመስላል ። ይኸውም አንደኛ አዘውትረን በምንጠቀምበት አማርኛ አልጫ ፣ ሲባል በርበሬ ያልገባበት ወጥ ማለት ሲሆን እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አነጋገር ግን አልጫ ሲል ጨው ያልገባ በት ወጥ ወይም ጣዕም የሌለው ምግብ ማለት ነው ። ለዚህም ማስረጃ ክርስ ቶስ ደቀ መዛሙርቱን በምሳሌ ሲያስ ተምራቸው "እናንተ የምድር ጨው ናችሁ ጨው አልጫ ቢሆን ግን በምን ይጣፍጣል ? ወደ ውጭ ተጥሎ በሰው ከመረገጥ በቀር ወደ ፊት ለምንም አይ ጠቅምም ሲል በማቴ. ም.5 ቁ 13 ተናግ ሯል ። ጨው የወጥን ጣዕም እንደሚያ ጣፍጥ ሁሉ ደቀ መዛሙርቱም በትምህ ርታቸው በጠቅላላው በመንፈሳዊ ተግባ ራቸው የሰው ልጆችን ኑሮ እንዲያጣ ፍጡ ሲመክራቸው መሆኑን እንረዳ ለን ።

እንግዲህ ወደ ዋናው አጠቃላይ ሃሳብ ስንመጣ አንድ ቤት ለማሠራት በቅድ ሚያ መሠረት ሲያስፈልግ ያ መሠረት የተጣለበት ቦታ ቤት ተብሎ የሚጠራው ደግሞ ግድግዳና ጣሪያ ሲሠራለት ነው። ያለበለዚያ ግን በመሠረቱ ብቻ ቤት ተብሎ ሊጠራ አይችልም ። እንደዚሁም ሁሉ አንድ ሰው ሃይማኖተኛ የሚባለው ስለተጠመቀ (ክርስቲያን) የሚል ቅጽል ስላገኘ ሳይሆን ሃይማኖት ከምግባር ጋር አጣምሮ ሲገኝ መሆኑን ቅዱሳት መጻ ሕፍት ይመሰክራሉ ።

ስለዚህም ሐዋርያው ቅ ያዕቆብ በመልእክቱ ሲያብራራ "ሃይማኖት አለኝ በጎ ሥራ ግን የለኝም የሚል ሰው ቢኖር ምን ይረባል ? ምንስ ይጠቅመዋል ? ሃይማኖቱ ብቻዋን ልታድነው ትችላለችን ? በጎ ምግባር የሌላት ሃይ ማኖት የሞተች ናትና ብቻዋን ልታ ድነው አትችልም ።አንድ እግዚአብ ሔር ብቻ ነው ብለህ በማመንህ መል ካም አድርገህ ነበር ። ነገር ግን በጎ ምግ ባር ካልጨመርክበት እንዲህ እንዳን ተስ አጋንንትም በግልጽ ያምኑበታል ። ስሙ ሲጠራም ይንቀጠቀጣሉ ። ዳሩ ምን ይሆናል በጎ ምግባር የላቸውምና አይድኑም አንተ ግብዝ ሃይማኖት ያለ ምግባር የሞተች እንደሆነች ልታውቅ ትወዳለህን ? ከወደድክስ የአብርሃም ሃይማኖት ፍጽምት ሆና የታወቀች ለት ልጁን ይስሐቅን ለመስዋዕትነት በማቅረቡ እንደሆነ እወቅ ተረዳ ። እም ነት ከሥራው ጋር አብሮ ያደርግ እንደ ነበረ በሥራም እምነት እንደተፈጸመ ተመልከት ይላል ። ያዕ. ም. 2 ቍ 14-23 ፤

አዎን አንድ ሰው በስም ሃይማኖ ተኛ ሆኖ በግብር ካልገለጸው ምን ይጠ ቅመዋል ? በጠቅላላው ሃይማኖታውያን እንዳይሠሩት በሕገ ወንጌል ጌታ ያዘ ዘውን ትእዛዝ የሚጥስ መጥፎ ሥራን የሚሠራ ከሆን አልጫ ነው ይባላል ። እንደዚሁ እያንዳንዱ ክርስቲያን ሃይማ ኖት እንኳን ቢኖረው በሥራ ካልገለ ጸው ከአጋንንት የተሻለ ሕይወት ሊኖ ረው አይችልም ። ምክንያቱም ሃይማ ትና ምግባር እንደ ነፍስና ሥጋ ተዋሕ ደው በአንድ ሰው ላይ ካልተገኙ ለየ ብቻ ከሆኑ የማይጠቅሙ ምውታንና አልጫ እንደሆኑ የተለያዩ መጻሕፍት ያስረዱናል ።

እንግዲያውስ እንደዚህ ከሆነ በአሁኑ ጊዜ ያለ ምንም ጉድለት የወንጌልን ትምህርት በግብር እያሳየን ሃይማኖት ከምግባር ጋር አጣምረን የምንገኘው ስንቶቻችን ነን? እስኪ ራሳችንን እንመ ርምር? በእውነት ስንቶቻችን በወንድ ሞቻችን ላይ በውሸት መስክረናል? ስን ቶቻችንስ ሰርቀናል ስንቶቻችንስ በጣ ዖት አምልከናል ? በጠቅላላው ስንቶ ቻችን በመጥፎ ተግባራችን ፍጡርንና ፈጣሪን አሳዝዝነናል መቾም ሕሊና ችን ይውቀሰን እንጂ እከሌ ተከሌ ተብ ሎ ሊቆጠር አይቻልም ።

አዎን ይህ ሁሉ በእውነተኛ ሃይማኖ ታውያን ሥራ ሲታይ ከንቱ ነው ይልቁ ንስ ይህ መጥፎ ተግባር መሆኑን ተገንዝ በን ሃይማኖት በበጎ ምግባር ካልለገ ጸዋት በሃይማኖት ብቻ የተስፋና የደስታ ዕረፍት ሊገኝ አይችልም ። ተተ ኪው ትውልድም መልካም ሃይማኖት እንዳለን አውቆ የሚከተለን ሕያው ማስ ረጃችን በጎ ምግባራችን ስለሆነች ሃይማ ኖትን ከምግባር ጋር እናጣምር ። እንላ ለን ።

ብርሃን ተድላ

---

ዶ ነው በማለት የሚያመሰጥሩት ይህኑ የወንዶችን የባላይነትና ጀብደኝነት አ ስወግደው እኩልነት እንዲሠፍን ለማ ድረግ ነው ።

ስለዚህ ሴቶችም ወንዶችም ሁሉም በክርስቶስ እኩል ናቸውና ባል [illegible] ን ፣ ሚስትም የባልዋን [illegible] ፈር መቆጠብ ይኖርባቸዋል የሀገሪቱ መምሪያ የኅብረተሰባዊነት ርእዮተ ዓ ለምና የሃይማኖታችንም መመሪያ የሚ ያስተላልፋት መልእክት ተመሳሳይነት ያለው ነውና ። ተግባባን ይሆን?

ቄስ መክብብ እጥናው



# መጽሐፍ ቅዱስና ልማት



ዘመናዊው ካህን ብራና ሲፍቁ ይታያሉ

ለአንድ ሀገር ከሚያስፈልጉት መሠረ ታውያን ነገሮች አንዱ ልማት ነው ። ልማት ሲባል በአጠቃላይ አነጋገር ለአንድ ሀገር ወይም ኅብረተሰብ ሥልጣኔና እድገት አማራጭ የሌለው እጅግ አስፈላጊና ተቀ ዳሚ ተግባር ነው ። የልማት ዕቅድ የሌላት ሀገር በአሁኑ ጊዜ ብትኖር በሥልጣኔ ወደ ኋላ መቅረቷን ብቻ ሳይሆን የዜጎቿ ህል ውና ወደፍጻሜ መቃረቡን ያሳያል ።

ሰው በዓለም ላይ ከተፈጠረ (ሥልጣኔ ከተጀመረ) ጀምሮ ከዓለም (ከተፈጥሮ) ጋር እየታገለ የሚኖር ፍጡር መሆኑ ግልጽ ነው ። ትግሉም በአንድ አቅጣጫ ወይም በአንድ ዓይነት ዘዴ ብቻ አይደለም ። ተፈ ጥሮ ከጊዜ ወደ ጊዜ በማያድርግ እንቅስ ቃሴ ይለዋወጣል ። ከተፈጥሮ የሚገኙ ጥሬ ሀብቶችም አብረው ከመለዋወጣቸው በላይ እያለቁና እያነሡ ይሄዳሉ ። ስለዚህ ሰው በምድር ላይ ለመኖር የተፈጥሮ ሀብ ቶችን በተለያዩ ዘዴዎችና በዘመናውያን መ ሣሪያዎች በመጠቀም አገልግሎት ላይ እንዲ ውሉ አድርጓል ፤ ያደርጋልም ። ይህም ከአ ምላኩ የተሰጠው ትዕዛዝና የተፈጥሮ ግዴ ታ መሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎ ይገ ኛል ። "በሕይወት ዘመንህም ሁሉ በድካ ም ከእርስዋ ትበላለህ ፤ .... ወደ ወጣህ በት መሬት እስክትመለስ ድረስ በፊትህ ወዝ እንጀራን ትበላለህ ፤ "(ዘፍ.3 ፡ 17. 19 የሚለው መለኮታዊ ኃይለ ቃል ይህንኑ የሚያስረዳ ነው ። ስለዚህም ማንኛውም ሰብአዊ ፍጡር በሕይወቱ ዘመን ሁሉ ምድ ር አልምቶ መጠቀም የተፈጥሮ ግዴታ ብቻ ሳይሆን ከእግዚአብሔር የተሰጠው ጸጋም ጭምር ነው ።

አሁን ያለንበት 20ኛው ክፍለ ዘመን የተግባረ እድ ሥልጣኔ በጣም የተስፋፋበት ጊዜ ነው።ዓለም በልማት በኩል ከተራ የእስ ተራረስ ዘዴ አልፋ በዘመናዊ የእርሻ ዘዴ ፤ በኢንዱስትሪና በፋብሪካ ወደፊት ትራመ ዳለች ። ሆኖም በአንጻሩ ተፈጥሮ በተለዋ ወጠ ቁጥር አዳዲስ ችግሮች በሰው ልጅ ላይ መድረሳቸው አልቀረም ። ሰውም በየ ጊዜው የሚደርሱበትን ችግሮች ለመቋቋም የተሻሻሉ ዘመናዊ ዘዴዎችን መጠቀም ግዴታ አለበት ፤ ከዘዴዎቹም አንዱና ዋነ ኛው የልማት ዕቅዶችን በየመስኩ መክፈት ነው ።

ምንም እንኳ የምግብ ጥናት ሊቃውንት በሚቀጥለው ክፍለ ዘመን ዓለምን ከባድ የረሃብ አደጋ እንደሚጠብቃት በመተን በይ ቢያስጠነቅቁም ፤ ዘዴ ሳይፈልጉ በስ ጋትና በፍርሃት መቀመጥ አያዋጣም ። ስለዚህ የልማት እንቅስቃሴን በማፋጠን የየሀገሩን ኢኮኖሚ ለማበልጸግና ምርትን ከፍ ለማድረግ የሚደረገው ጥረት በሰፊው ቀጥሏል ።

ልማት ለአንድ ሀገር ዜጐች በአጠቃ ላይ የሚያስፈልግ መሆኑ ግልጽ ነው ፤ ስለ ሆነም የተወሰኑ ክፍሎች ብቻ የሚሳተፉ በት ተግባር አይደለም ። እያንዳንዱ ግለ ሰብና ኅብረተሰብ በልማት ሥራ መሳተፍ የህልውና ግዴታ ነው ።

"መጽሐፍ ቅዱስና ልማት" የሚለውን ርእስ አንባቢው ሲመለከት ሁለቱን ምን አገናኛቸው ? የሚል ጥያቄ በአእምሮው ሊነሣ ይችላል ። ሆኖም ስለአለመገናኘቱ ተወት አድርገን መጽሐፍ ቅዱስ ስለልማት ምን ይላል ? የመጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች ልማ ትን እንዴት ይመለከቱታል ? በሚለው አቅጣጫ በመጠኑ ለማስረዳት እንሞክራ ለን ።

እግዚአብሔር ለሰዎች ይመሩበት ዘንድ



www.ethiopianorthodox.org

ቃሉን በቅዱሳኑ በኩል አስተላልፏል (ሰጥቷል) ። ይኸውም የክርስትና እምነት (ሕይወት) መሠረታዊ መመሪያ የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ነው ። ይህ ቅዱስ መጽሐፍ ክርስቲያኖች ሁሉ መንፈሳዊ ሕይወታቸውን የሚመሩበት የእግዚአብሔር ቃል ነው ። ይሁን እንጂ መመሪያነቱ ለመንፈሳዊ ሕይወት ሳይሆን ለሥጋዊ ሕይወትም ጭምር ነው ።ለሥጋዊ ኑሮ አስፈላጊውን ነገር ሁሉ ይገልጻል ። ስለዚህ ለሰዎች (ለክርስቲያኖች) ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው መመሪያ መንፈሳዊውንና ሥጋዊውን ኑሮ በትክክል ለመምራት የሚያስችላቸው ፍጹም ሕግ ነው ።



ካህኑ ወንበር ሲሠሩ

መጽሐፍ ቅዱስና ልማት ስንል ፣ ሰው ሁለቱን አጣምሮ በተገቢው መንገድ ሕይወቱን መምራት እንዳለበት መግለጻችን ነው ። ክርስቲያን በቃሉ ሕያውነት አምላኩን እያመሰገነ በልማት ሥራ በመሳተፍ "... ሊሠራ የማይወድ አይብላ ..." ያለውን የእግዚአብሔር ትዕዛዝ መፈጸም እንደሚገባው ለማስረዳት ነው ። መጽሐፍ ቅዱስና ልማት ስንል ፣ የእግዚአብሔር ቃል ያረቅ ሕይወትን አለሰልሶ ነፍስን እንደሚያረካ ፣ የልማት ሥራ ምድርን አለምልሞ ሰዎችን እንደሚያጠግብ ማሳሰባችን ነው ። "ምድሩን የሚሠራ ሰው እንጀራ ይጠግባል ፤" ይላልና ። (ምሳ. 12 ፥11) ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው ማንም ቢሆን ለራሱና ለኅብረተሰቡ ብልጽግና በሚበጀው የልማት ሥራ መሳተፍ ተገቢና ሰብአዊ ግዴታው ነው ። የልማት ሥራ መፋጠን ከሚደርሰው የኢኮኖሚ ቀውስ ያድናልና። ስለዚህ የልማት እንቅስቃሴ መጠናከር ለኅብረተሰቡ ኑሮ ዋስትና ነው ።

ከልማት ውጤት የሚገኘው ምርት ከፍ ሲል ሀገር ትበለጽጋለች ፣ በዚህ አንፃር የመጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች በልማት ሥራ ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ አላቸው ። መመሪያቸው መጽሐፍ ቅዱስ ልማትን በሚመለከት ጉዳይ ፦ "... እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ወስዶ ያበጃትም ይጠብቃትም ዘንድ በዔደን ገነት አኖረው ። (ዘፍ.2 ፥ 15) የሚደክመው ገበሬ ፍሬውን ከሚበሉት መጀመሪያ እንዲሆን ይገባዋል ።

(2ጢሞ.2 ፥ 6) ስለሚል ግንባር ቀደም አልሚዎች መሆን ይገባቸዋል ።

ለምሳሌ ፦ በቅርቡ የሀገራችን የልማት ዘመቻ ታውጆአል ፣ ይህ የልማት አዋጅ በተግባር ሲተረጐም ለሀገሪቷ ኤኮኖሚ መገንባት ትልቅ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት ይጠበቃል ።

ሕይወቱ በአምላኩ መመሪያ የተመሠረተ ክርስቲያን በዚህ የልማት ሥራ ደጋፊ ብቻ ሳይሆን ግንባር ቀደም ተሳትፎ የሚያደርግ ነው ። ሌላው ክፍል ቀስቅሶት ሳይሆን ራሱ አስቦ ድርሻውን ማበርከት ይገባዋል።

መጽሐፍ ቅዱስ በልማት ሳይሳተፉ መኖርን አያስተምርም ። መጽሐፍ ቅዱስ የልማት ጐታች ወይም (በጊዜው እንጋገር) አድኃሪ የሚመስላቸው አንዳንድ ግለሰቦች ይኖሩ ይሆናል ። ለእነርሱ እንደመሰላቸው መጽሐፍ ቅዱስ በልማት የሚገኘውን ሥልጣኔ ወደኋላ የሚጐትት መመሪያ አይደለም ። "ሊሠራ የማይወድ አይብላ'..." እያለ የሚያዝዝ ሕያው ቃል ነው እንጂ ። ታዲያ ይህን ኃይለ ቃል ማመን ያቅታቸው ይሆናል ፤ ይሁን እንጂ አመኑም ካዱ ከብዙ ሺህ ዓመታት በፊት ከእግዚአብሔር የተሰጠ ሕያው ቃል መሆኑን ሊረዱት ይገባል ።

በሌላ በኩል ደግሞ እጃቸውን አጣምረው መቀመጥ የለመዱ ፣ ልማትን ወደ ጐን ትተው መጽሐፍ ቅዱስን እንከተላለን የሚሉ አንዳንድ ግለሰቦች አይጠፉም ። እነዚህ በሀገር ልማት ሳይሳተፉ የልማት ውጤት የሆነውን እንጀራ የሚበሉ ንጹሑን ቃለ ሕይወትና እውነተኛ ተከታዮቹን የሚያሰድቡ ዋልጌዎች ናቸው ። ስለዚህ ሳያለሙ የለማውን በመሳተፍ የሚኖሩ የልማት ጠንቆች የመጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች ነን ቢሉ ፤ መጽሐፉ የሰነፎችና የሥራ ፈቶች ማመካኛ ባለመሆኑ አይደላችሁም እንላቸዋለን ።

እንዲሁም በሀገር ልማት ለመካፈል የማይፈቅዱ የእምነት ክፍሎች አሉ ይባላል ። ይህ ምን ያህል እውነት እንደሆነ ባይታወቅም ፤ በዚህ አጋጣሚ በአንዳንድ ዓላማ ቢሶች ሰበብ የእምነት ሰዎች (መጽሐፍ ቅዱስ) የልማት ዕንቅፋት ነው ሊባል አይችልም ። የዚህ ዓይነቶች መጽሐፍ ቅዱስን ጨርሰው ገልጠው የማያውቁና ቢገልጡም እንኳ ይዘቱ ያልገባቸው አስመሳዮች ናቸው ። ታዲያ በነዚህ የእምነት ጥገኞች ስህተት የተነሣ አንዳንድ የዋሆች መጽሐፍ ቅዱስን ያለቦታው ሲጠቅሱና ሲነቅፉ ይሰማሉ ። "መጽሐፍ ቅዱስ መና ከሰማይ ያወርዳል ፤ ቁጭ ብላችሁ የሰማዩን ወፎች ተመልከቱ ... ወዘተ " ይላል በማለት እንደመሰላቸው በመተርጐም የልማት ሥራን እንደ ማይደግፍ አድርገው ይጠቅሳሉ ። ይህም ቢሆን የመጽሐፍ ቅዱስን ዓላማና አተረጓጐም አለመረዳት ስለሆነ የዋህነትን ብቻ ሳይሆን ያላዋቂ ተቺነትን ያመለክታል ።

በመሠረቱ መጽሐፍ ቅዱስን ካልካዱ በስተቀር በጥንት ዘመን የመና መውረድ (መዝነም) እርግጠኛነት አያከራክርም ። ለእሥራኤላውያን መና (ኅብስተ - ሰማይ) የወረደላቸው በምድረ በዳ በጉዞ ላይ እንዳሉ ነበር ። ታዲያ በዚያን ጊዜ በበረሃ ቃጠሎና በረሃብ ሲጨነቁ ከባርነት ነፃ ካወጣቸው አምላካቸው መናን መጠበቅ አማራጭ የሌለው ግዴታ ነበር ። የሲናን ምድረ በዳ አለትና አሸዋ ሊያለሙ አይችሉም ነበርና ። ከዚህም ሌላ የመናው መውረድ በእግዚአብሔር ዓላማ ውስጥ የተለየ ቦታ ፣ ምክንያትና ጊዜ ነበረው እንጂ እንዲሁ በአጋጣሚ የሆነ አይደለም ። ቢሆንም መናውን ሠርተው እንጂ እንዲሁ ቁጭ



ካህናት በልማት ሥራ ተሠማርተው ሲቆፍሩ

ብለው አልተሰጣቸውም ። የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል ብናስታውስ (ዘጸ. ምዕ. 16 ፥ ቁ 4.5. 16 እና 21) እያንዳንዱ ቤተሰብ ለየዕለቱ የሚበቃውን መና ጧት ጧት በብርድ ወጥቶ መልቀም ነበረበት ። እዚህ ላይ ዓላማችን ስለመና መውረድ ለማተት አይደለም ። ስለ መጽሐፍ ቅዱስና ልማት የሚሰጠውን እውነት - አልባ ትችት ግልጽ ለማድረግ እንጂ ፤ መጽሐፍ ቅዱስ መና ለእሥራኤል ወርዶ ነበርና አሁንም ቁጭ ብለህ በማንጋጠጥ መና እንዲወርድልህ ጠብቅ ያለበት ቦታ የለም ። ጥረህ ግረህ ፤ ለፍተህ አልምተህ ፤ በፊትህ ወዝ እንጀራህን ብላ ፤ ይላል እንጂ፤አንዳንዶቹ ግን እጃቸውን ወደ ልማት ሥራ መዘርጋት ሲሳናቸው በማመካኘት ስለመና መውረድ ያወራሉ ። ስለዚህ የልማትን ሥራ በጣታቸው መንካት ሳይፈልጉ መናን የሚጠብቁ በዋልፈሰሶች ስለመና መውረድ እያወሩ መጽሐፍ ቅዱስን ቢተቹ አይደንቀንም ።

ሌላው ደግሞ "ወደ ሰማይ ወፎች ተመልከቱ..." የተባለው እምነቱን በአምላኩ ላደረገ ክርስቲያን ጭንቀት እንደማይገባው የሚያስረዳ እንጂ እጅ አጣጥፎ መቀመጥን አያመለክትም ። እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ሁሉ መልካሙን እንደሚያስብ እናምናለን ። ሰው ከሰማይ ወፎች የበለጠና የተሻለ ነው ፤ ከእንስሳትና ከዕፀዋት የተለየ የእግዚአብሔር ክቡር ፍጡር ነው ። በመሆኑም ከሌላው ፍጥረት ሁሉ አብልጦ አምላኩ እንደሚያስብለት ነው ጥቅሱ የሚያብራራው ። እንዲህ ስለሆነ ሰው መሥራት እንጂ መጨነቅ የለበትም ። ስለሆነም ያለ ጭንቀት ተፈጥሮን አልምተን መጠቀም ተገቢያችን ነው ።

እንግዲህ መጽሐፍ ቅዱስና ልማት ሲባል ምን ያህል አብረው እንደሚሄዱ ተመልክተናል ። መጽሐፍ ቅዱስ የመንፈሳዊ ሕይወት መመሪያና መበልጸጊያ እንደሆነ ሁሉ ፤ ልማት ለአንድ ሀገር ዕድገትና ብልጽግና መሠረት ነው ። መጽሐፍ ቅዱስ (ቃሉ) ለሕይወታችን (ለነፍሳችን) ፤ ልማት ለሀገራችን ብልጽግና እኩል አስፈላጊዎች ናቸው ። ያለመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ነፍስ ትመነምናለች ፤ ያለልማት ሀገር ትደኸያለች ፤ ትራባለች ።

በአጠቃላይ መጽሐፍ ቅዱስ ሕያው ቃል መመሪያችን ሲሆን ልማትን የሚያግፍ እንጂ የልማት እንቅስቃሴን ወደኋላ እንደማይጐትት እናረጋግጣለን ። የመጽሐፍ ቅዱስ ተከታይ መሆንም ከልማት ሥራ ወደኋላ አያሰኝም ። ስለዚህ በአንዳንድ ግለሰቦች አስተሳሰብ ከልማት ሥራ መለየት የቃሉ ተከታይ አያሰኝም ። ስለሆነም ከልማት ውጤት የሚገኘውን ፍሬ ለማየት በልማት እንቅስቃሴ በመሳተፍ በብርቱ መድከም አለብን ። "በልቅሶ የሚዘሩ በደስታ ይለቅማሉ .... ነዶአቸውን ተሸክመው ደስ እያላቸው ይመጣሉ ። " ይላልና (መዝ.125 ፥ 5. 6) ።

ተስፋዬ ረጋሣ

# ዐሥራ ሦስት ኤጲስ ቆጶሳት

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ለመጀመሪያ ጊዜ በሕዝብ ምርጫ 13 ኤጲስ ቆጶሳትን መርጣ ሾመች ። ምርጫው ከአዲስ አበባና ከየክፍላተ ሀገሩ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ስም በተወከሉ ካህናትና በሰበካ ጉባኤ አባላት እንደዚሁም በቅዱስ ሲኖዶስ ተፈጽሞአል ። የምርጫው አፈጻጸም በትክክለኛ ዲሞክራሲያዊ ሥነ ሥርዓት እንደተካሄደ



የምርጫው አፈጻጸም ፣

በምእመናንና በተመልካቾች ዘንድ ግምት ተሰጥቶታል ። በሌላ በኩል ታዛቢዎች እንደሚሉት ከምእመናት ሴቶች መካከል አንዲት ሴት እንኳ ለመምረጥ በሴቶች በኩል ስለአልተወከለች "ክርስቲያን ሴቶች የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ለመምረጥ መብት የላቸውምን" የሚል ጥያቄ ከአንዳንድ ግለሰቦች ተሰምቷል ወደፊት ግን ማስተዋልን በተሞላ ጥንቃቄ እንደሚታሰብበት ሳናስገነዝብ አናልፍም ።

የ13ቱ ኤጲስቆጶሳት ሥርዐተ ሢመት የተፈጸመው ጥር 13 ቀን 1971 ዓ.ም. በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ አንብሮተ እድ ነበር ። በሥርዓተ ሢመቱ ጊዜ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ጓድ ዶክተር ዓለሙ አበበ ፤ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ምእመናትና ምእመናን ፤ የአ

ወደ ገጽ ፩ ዞሯል






www.ethiopianorthodox.org

… ህብር ።

አብያተ ክርስቲያናት ለክርስቶስ ቃ
ል ምንጭ ከመሆናቸውም በላይ ለብዙ
ኃኑ ሕዝበ ክርስቲያን የሚያቀርቡትን
የሕይወት መንገድ የማያቋርጥ ጥሪ
ሆነ በየጊዜው መንግሥተ ሰማያት ቀር
ባለችና ንስሃ ግቡ በማለት የሚያስተ
ጋቡት የንስሃ ጥሪ ደወላቸው ከእንቅ
ልፉ ነቅቶ ለሚመጣ ምእመን ሁሉ የጽ
ድቅ ፍሬ እያፈራ አሁን ተሰውራ ያለች
ኋላ የምትገለጠው መንግሥተ ሰማያ
ትን ለማውረስ የሚያበቁ ወደ ዘላለ
ማዊ ሕይወት የመሸጋገሪያ ቅዱሳን ድ
ልድዮች ለመሆን በየአቅጣጫው ታንጸ

… ነው መድኃኒም በክ
ርስቶስ ነው በማለት በራቸውን ከፍተ
ው መንፈሱና ሙሽራይቱ ና ይላሉ የሚ
ሰማም ና ይበል የተጠማም ይምጣ
የወደደም የሕይወትን ውኃ እንዲያው
ይውሰድ የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ''
ይላሉ ።

ከእነዚህ መንፈሳውያን ማኅበራት
አንዱ የሆነው መቀሌ ቅድስት ድንግል
ማርያም ቤተ ክርስቲያን የሚገኘው የክ
ርስትና መሠረትና ፈር በሆኑት በአቡ
ነ ሰላማ (ፍሬምናጦስ) ስም ከሣቴ ብር
ሃን ሰላማ የወላጆችና የተማሪዎች የመ
ጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ተብሎ የተሰየ
መው ስብከተ ወንጌል ኦርቶዶክሳዊ
ማኅበር ነው ።



የከሣቴ ብርሃን ሰላማ የመ/ቅዱስ ማኅበር ወጣቶች

ዋል የተራራ ላይ የመቅረዝ መብራትም
ሆነዋል ።

በዘመናችን ብዙ የመንፈሳውያን ማ
ኅበራት የፈጣሪን ቃል ለሚራቡ ጽድ
ቅን ለሚጠሙ ሁሉ ማንም የተጠማ
ቢኖር ወደእኔ ይምጣና ይጠጣ በማለት
ቸርነቱ ወደማያልቀው አምላክ በማቅ
ረብ በቅዱስ ሕይወት በኪዳነ ቃሉና
በሕገ ወንጌሉ ነፍሳትን ለማነፅ ''ዓለ
ሙም ምኞቱም ያልፋሉ የእግዚአብሔ
ርን ፈቃድ የሚያደርግ ግን ለዘለዓለም
ይኖራል ፤ በኢየሱስ የሚያምን የዘላለም
ሕይወት አለው ፤ በልጁ የማያምን ግን
የእግዚአብሔር ቁጣ በእርሱ ላይ ይኖ
ራል እንጂ ሕይወትን አያይም እነሆ

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ዘወ
ትር ቅዳሜ ለወጣቶች እሁድም ለወላ
ጆች በጠቅላላ ከ250 - 350 ብዛት ላላ
ቸው አባላት በሚገባ በምርጥ ሰባክያን
ቃለ ክርስቶስን ያስተምራል ይህ ማኅ
በር ሥርዓተ ቅዳሴን ግዕዝን ለወጣ፡
ትውልድ በማቅረብ የአባቶች የአበው
ቅዱሳንና የሐዋርያት ትምህርትን በመ
ስጠት ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን በሚገ
ባ ያስጠናል ማኅበሩ በአባል መዘምራኑ
ልብን የሚመስጡ መንፈሳውያን መዝ
ሙሮች፣ጥልቅ ምስጢራዊ ስብከቶች በ
ምርጥ ሰባክያኑ ግሩም ድንቅ የሆኑ መ
ንፈሳውያን ትርኢቶች ሐዋርያዊ መልእ
ክቶችና ሥነ ጽሑፎች በአባላቱ በፕሮ

ግራም እያዘጋጀ ለሕዝበ ክርስቲያኑ
በብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ድጋፍ በተሠራ
ለት ዘመናዊ አዳራሹ ያስተናግዳል ይህ
ማኅበር በየዓመቱ የሚያገለግሉትን መ
ሪዎች እየመረጠ በሚገባ ክርስቲያና
ዊ ግዴታው ተልእኮውን በመ
ወጣት ላይ ይገኛል ። ማኅበሩ በትም
ምህርት አሰጣጡ በጣም ሲደነቅ ወላጆ
ችና ወጣቶችን አስተባብሮ በመያዝ ሁ
ለቱን አቅፎ በመገኘቱ እጅግ ያስደስ
ታል ከሣቴ ብርሃን ስብከተ ወንጌል ያለ
ው ቅዱስ ይዞታ አጥጋቢ ከመሆኑም
በላይ ተደራጅቶ በመጠናከር ላይ ላለው
የመቀሌና አካባቢዋ አብያተ ክርስቲያ
ናት የሰበካ ጉባዔ ማዕከላዊ ጽ/ቤትና
የተሐድሶው መድረክ በቅርቡ ይሆናል
ብለን በታላቅ ክርስቲናዊ ጉጉት የምን
ጠብቀው የ17 ዓመት ባለዕድሜ ማኅ
በር ነው ።

የጌታችን የልደት የስቅለትና የትን
ሣኤ በዓላት ሲደርሱ የመቀሌ ሕዝበ ክ
ርስቲያን በቀጥታ ወደ ማኅበሩ አዳራሽ
በመሄድ የልደት ፣ የስቅለት ፣ የትንሣኤ
መንፈሳውያን ትርኢቶችን በየዓመታ
ቱ በጥልቅ ትዝታ ይመለከታል የማኅበ
ሩ አባላት ማኅበሩ የሚሰጣቸውን ትም
ህርት ከልብ በማሳደር ትህትናና ግብረ
ገብ ገንዘባቸው ሆኖ አብዛኞቹ አብርሃ
ማዊ ዕምነት ይስሐቃዊ ታዛዥነት ያዕ
ቆባዊ ሂሩት ኢዮባዊ ትዕግሥት ዳዊ
ታዊ ቅንነትና ሙሴያዊ የወገን ተቆር
ነት ፣ አገር አቀፍ ወዳድነት መለያ
አርማቸው ነው ። ማኅበሩ በተለይም
ለወጣቶች የቤተክርስቲያኒቱና የአገ
ራቱ ተቆርቋሪዎች እንደሆኑ ተቀዳሚ
ዓላማው ነው እጅግ በርካታ ወጣቶችን
በሃይማኖት ኮትኩቶ በግብረገብ አንፆ
ያሳድጋል ሆኖም ማኅበሩ ይህን ሁሉ
ተግባር ሲያከናውንና ከፍተኛ ግልጋ
ሎት ሲሰጥ ረዳት አባላቱ ብቻ ናቸው
ይህም ማኅበሩ የሚያገኘው ገቢ ከሚያ
በረክተው ፍሬ ጋር ሲነፃፀር ገቢው እጅ
ግ አነስተኛ ነው በተለይም ወጣት መዘ
ምራን ያለአንዳች የመዝሙር መሣሪያ
ና ልብስ ሲዘምሩ ማየት እጅግ ያሳዝ
ናል መንፈሳዊ ሕይወት የሚያድስ መ

ወደ ገጽ ፳፱ ዞሯል



# የሴቶች ዐምድ

የእናቶች ጀግንነት በአድዋው ጦርነት

እንዲህ እንደአሁኑ ሥልጣኔና ዕው
ቀት ባልተስፋፋበት ዘመናዊ የጦር ስል
ት ከውጭ እንጂ ከእኛ በሌለበት ከልዩ
ልዩ ክፍል የወጡ ባለሙያዎች ባልበዙ
በት በአድዋ በተደረገው ጦርነት እና
ቶች ያበረከቱት ድርሻ እጅግ ከፍተኛ

ቆርቆር በአድዋ የነበረውን ጠላት ለመ
መለስ ተባባሪዎች ሆነዋል ።

ሥልጣኔው ተንሰራፍቶ ትራንስፖ
ርት በሌለበት ሠራዊት እየተመመ ነጋ
ራቱ እየተጐሰመ አፄ ምኒልክ በሚጓዙ
በት ጊዜ በእግር በፈረስ ከሚጓዘው ወ
ታደር ጋር አብረው ዘምተዋል ። በዚያ
ለተሰለፈው ወታደር ድሎት ባያስፈልገ

ቹ ደግሞ ጠጅ የተሞላበት ቀንድ ፣ እን
ጀራ ሙሉ የሆነ መሶብ ተሸክመው አብ
ረው ወደ ጦርነቱ ሥፍራ ተጉዘዋል ።
ይኸም ብቻ ሳይሆን ወንዱ ድንኳን ሲ
ተክል እንጨት ሲፈልጥ ጋግረውና
ቀድተው ምግብ አዘጋጅተው ያን ሁሉ
ሠራዊት የሚመግቡ እናቶቻችን ነ
በሩ ።
በምግብ ማዘጋጀት ብቻ ሳይሆን እን



የኢትዮጵያ ጀግኖች ሴቶች

ነበር ።

ሀገርን የመውደድ ወኔ ስለነበራቸው
የማንም አስገዳጅነት ወይም ገፊነት
ሳይኖር ሴትነታቸው ምክንያት ሆኖ እ
ራሳቸው ወይም ሌሎች ወደኋላ ሳይጐ
ትቷቸው በሀገር ቀልድ የለምና ድንበር
ሲነካ ወገን ሲደፈር ለፆታቸው ልዩነትና
ትርጉም ሳይሰጡት የቀድሞዎቹ እናቶ
ቻችን ጠላት ሀገራችንን ሲደፍር በመ

ውም ያለምግብ ለመዋጋት ስለማይ
ችል በምግብ በኩል ያለው መሰናዶ በእ
ናቶቻችን ላይ የተጣለ ነበር እንጂ እንደ
ዛሬው በአይሮፕላን ተጭኖ በጊዜው
የሚደርሰው የታሸገ ምግብ አይገኝም
ነበርና ጀግኖች እናቶቻችን ምጣድ ከነ
አክባሎው በእራሳቸው እንስራና ገንቦ
በጀርባቸው የማሰሻ ጩርቃቸውን ከነ
ጥፍጥሬያቸው በእጃቸው ሲይዙ ግማሾ

ደአሁኑ የጤና ጥበቃ ባለሙያዎች ስለአ
ልነበሩን የጤና ጥበቃውም ሥራ የሚካ
ሄደው በጀግኖች እናቶቻችን ስለነበር
የታመመውን አስታመው የወደቀውን
አንስተው የቆሰለውን በሚያውቁት
የሀገር ባህል ዘዴያቸው በማሰሻ ተኩ
ሰው የተሰበረውን ጠግነው ፣ የነደፉ
ትን ጥጥ ነጠላና ቀሚሳቸውን ሳይቀር
ለሕክምና አገልግሎት በማዋል በጦር



www.ethiopianorthodox.org

# ሲ ኖ ዶ ስ ና ት ር ጕ ሙ

ሲኖዶስ ማለት ምን ማለት ነው ? ሲኖዶስ ማለት ቃሉ ግሪክኛ ሲሆን ትርጓሜውም ስለ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን የሚሰበሰቡ የማኅበረ ክርስቲያን ፤ የካህናትና የጳጳሳት ጉባኤ ማለት ነው ።

ሁለተኛም ይህ ጉባኤ የጻፈውና የወሰነውን ሕግ ሥርዓትንና ቀኖናን ፤ ሃይማኖትንም የያዘ የጉባኤ መጽሐፍ ስም ነው ።

ሲኖዶስ መቼ ተጀመረ ? እንዴት በምን ለምን ? ተጀመረ ?

ሀ ሲኖዶስ የተጀመረው በሐዋርያት ዘመን ነው ይሁን እንጂ በሐዋርያት ዘመን የነበረው ሲኖዶስ የመጀመሪያው ስብሰባ ከሐዋርያት ማኅበር በወጣው በይሁዳ ምትክ ሌላ ሐዋርያ ለመምረጥ ሲሆን በዚህ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን መካከል የበላይ አዛዥ ሹም አልነበረም ። ሐዋርያትም በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ብቻ የቤተ ክርስቲያን ጠባቆች ነበሩ ይኸውም «ከናንተ መካከል የበላይ ወይም ታላቅ መሆን የሚፈልግ ቢኖር ለናንተ አገልጋይ ይሁናችሁ መምህራችሁ አለቃችሁ አንድ ኢየሱስ ክርስቶስ ነውና» የሚለውን መለኮታዊ ቃል በማሰብ ሥልጣንን ክብርን የመመኘት አሳብ ከልባቸው ስለተወገደላቸው ትሕትናን እንደመጨረሻ ክብር ቆጥረው ተቀበሉት ። ይሁን እንጂ ከጥቂት ጊዜ በኋላ የክርስቲያን ቁጥር እየበዛ ስለሄደ ለሁለተኛ ጊዜ ስብሰባ (ሲኖዶስ) አድርገው ስለገንዘብ አያያዝና ስሬ አስተዳደር በሐዋርያት ምክር ፯ ዲያቆናትን ለአገልግሎት ከማህበሩ መካከል መረጡ ። እነዚህም የተመረጡ ፯ቱ ዲያቆናት መንፈስ ቅዱስንም ጥበብንም የተመሉ ነበሩ ። የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ገጽ ፹፮-፹፯ ።

ለ ከሐዋርያት በኋላ እስከ ፪፻፶፩ ዓመት ድረስ በክርስቲያኖች ላይ መከራና ስደት ተፈርዶባቸው ነበር ። ነገር ግን ከዚህ በኋላ በጋሎስ ዘመነ መንግሥት ለጥቂት ዓመታት ያህል ዕረፍት አገኙ ።

ሐ ከ፪፻፶፫ ጀምሮ እስከ ፫፻፭ ድረስ ፲፪ ነገሥታት ነግሠዋል ይህ ዘመን ክርስቲያኖች ያለቁበት ዘመን ስለሆነ ዘመነ ሰማዕታት ተብሎ ተጠራ ምክንያቱም በዘመኑ መጻሕፍትም አብያተ ክርስቲያናትም በእዋጅ እንዲቃጠሉ እንዲጠፉ ከመደረጉም በላይ ክርስቲያኖች ሁሉ ጣኦትን እንዲያመልኩ ባያመልኩ ግን ከሹመታቸው እንዲሻሩ ከክብራቸው እንዲዋረዱ ባሮችም ሆነው እንዲሸጡ እንዲገደሉ ይህ የንጉሡ ትእዛዝ በአዋጅ እንዲነገር ተደረገ(ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ገጽ ፶፱-፶፬) ።

መ ካህናት ወይም ቀሳውስት በየቤተ ክርስቲያኑ ኃላፊነት ተቀብለው የተሾሙ ሁሉ ከ፫፻፲፭ ዓ.ም. በኋላ በሶስት ዓይነት ስሞች ይጠሩ ጀመር ፩ኛ ቄስ (ጳይ ሚን) በመባል የተለየ የመንጋ ጠባቂ ማለት ነው ። ፪ኛ ጵርስቢ ትሮስ ተባለ ሽማግሌ ማለት ነው ፫ኛ ሜትሮጳሊስ ተባለ እጲስ ቆጶስ ማለት ነው ። ይኸውም በዮናኒ ማለት በግሪክኛ ቋንቋ ነው እነዚህም በዚህ ስም የሚጠሩት በሮም ከተማ በአንጾኪያ በእስክንድርያ በኤፌሶን በቆሮንቶስ የሚቀመጡት ብቻ ናቸው ።

ሠ. ከዚህ በላይ በተጻፉት በአምስቱ ከተማዎች የሚኖሩትን ምእመናን በሚያስተዳድሩ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከክርስቶስ ልደት በኋላ በቀጳዶቅያ ከ፪፻፶ ዓመት ጀምሮ ይላድስ በምትባል ከተማ ሲኖዶስ ከፈቱ ከዚህ በኋላ ሲኖዶስ በየጊዜው ስብሰባ እያደረገ ለተቸገሩት አብያተ ክርስቲያናትና በስደት ለተበተኑ ክርስቲያኖች ሁሉ አስተዋጽኦ እያደረገ ረዳ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ገጽ ፶፶፱-፩፻፷ ።

ረ ከክርስቶስ ልደት በኋላ ከላይ በተጠቀሰው ዘመን በተደረገው ሲኖዶስ ስብሰባ የሮም ኤጲስ ቆጶስ ቆጵርያኖስ የሚባለው በሐዋርያው በቅዱስ ጴጥሮስ ወንበር የተቀመጠ ከቀሩት ኤጲስ ቆጶሳት ሁሉ በላይ መሆን አለበት ሲል አንተ ኰኵሕ ወዲበ ዛቲ ኰኵሕ አሐንፃ ለቤተ ክርስቲያን ያለውን ቃል ማስረጃ አድርጎ ጽፎ ለሲኖዶሱ አቀረበ ይላል (ስለቤተ ክርስቲያን አንድነት በጻፈው መጽሐፉ ገጽ ፪፻፷፩ ።

ሰ ከላይ በመ ተራ ቁጥር እንደተጻፈው ከሐዋርያት ዘመን በኋላ የሲኖዶስ ሥርዓት ጥቂት በጥቂት በሐዋርያት ዘመን የነበረው የእኩልነት ሥርዓት ወደ ገዥና ወደ ተገዥነት ሥርዓት እየተለወጠ ሄደ ይኸውም ስለ ሲኖዶስ በሚሰበሰቡበት ጊዜ ለሲኖዶሱ የበላይ ሰብሳቢ አልነበረም በዚህ ጊዜ ግን ጉባኤውን የበላይ ሆኖ የሚመራ አንድ ሰው አስፈላጊ መሆኑን ስለምረጥ ስለተስማሙ መረጡ ይህ ከጉባኤው መካከል ለመሪነት የሚመረጠው ሰው ከቀሳውስትም ቢሆን ከሕዝብም ቢሆን ልዩነት አልነበረውም በኋላ ግን ከሕዝብም ሆነ ከቀሳውስት ወገን ቢመረጥ የቤተ ክርስቲያን ጠባቂ ነውና ኤጲስ ቆጶስ ተብሎ መሾም ይገባዋል ተብሎ ተወሰነ ።

ቀ ይህ የተመረጠው ኤጲስ ቆጶስ ለጥቂት ዓመታት ከሠራ በኋላ እንደገና ሥርዓት እየሰጠ ከጉባኤ ጋር ተስማምቶ ለወጠው ይኸውም ፩ኛ ሰባሳቢውን እንደ አሮን ልጅ እንደ ብሉይ ሊቀ ካህናት ማዕረግ ስለሰጠው ከካህኑም ሆነ ከሕዝብ ተለየ ። ፪ኛ ቀሳውስትን እንደ ብሉይ ካህናት ደረጃ ስለሰጣቸው ከሕዝብ ተለዩ ፫ኛ ዲያቆናትን እንደ ሌዋውያን ደረጃ ማዕረግ ስለሰጣቸው ከሕዝቡ ተለዩ ፬ኛ መጽሐፍ አንባቢዎች ፭ኛ መናፍስትን በጸሎት ከሰው የሚያወጡ ኢክሶርኪስቻን ፮ኛ የኤጲስ ቆጶስ ተከታዮች ፯ኛ በረኞችና ጠራጊዎች ብሎ ደረጃ በደረጃ ሾመ ከዚህ በኋላ በታላቁ ቈስጠንጢኖስ ዘመን አብያተ ክርስቲያናት የትረጎዋ አብያተ ጣኦታት ይትዐጸዋ ብሎ አዋጁን ባዋጁ ከመመለሱም በላይ የክርስቲያን መሪዎች በየፍርድ ቤቱ እየተቀመጡ እንዲፈርዱ የቀኙ መንበር ስለተፈቀደላቸው ይህንኑ መነሻ በማድረግ ፍትሕ መንፈሳዊ ፍትሕ ሥጋዊ ብለው ሁለት ክፍል አድርገው ፍትሐ ነገሥት የሚለውን መጽሐፍ ፫፻፲፰ቱ ሊቃውንት ጽፈዋል ከ፴፪ ዓ. ም. በኋላ ይህ የሲኖዶስ ጉባኤ ቀስ በቀስ መንፈሳዊ ሥራውን ወደ ሥጋዊ ስለ ለወጠ በዚህ ምክንያት የጳውሎስን ነገር አስቦ እንዲህ ሲል ጻፈ «እላንት በዋጋ ተገዝታችኋልና ለሰው ባሮች አትሁኑ (ዮሐ.፲ ፴-፳፥፩ ቆሮ.፯.፳፫) አሁንም በሲኖዶስ የተሰበሰቡ ኤጲስ ቆጶሳት ሁሉ በክርስቶስ ስም ያልተሰበሰቡ የመንፈስ ቅዱስንም ፈቃድ ያልጠየቁ ብዙ ጊዜም በክርስቶስ ስም መጥተው በነበሩ በቅዱሳን ወንድሞቻቸው ላይ የበረቱ በመሆናቸው እንዲህ ያለው ሲኖዶስ ቃሉን እንደ እግዚአብሔር ቃል ያስቆጥር ዘንድ የሰውን ሐሳብና ትምህርት ሁሉ ለቃሉ ለሥልጣኑ ያስገዛ ዘንድ በወደደ ጊዜ ትዕቢተኛ በመሆን ወደ ስህተት ጉድጓድ ወደቀ ይላል» የሲኖዶሱንም ቃልና ትእዛዝ ይሰበ[illegible] የነበረ ዲዮናስዮስ እክሲጉውስ የሮም መነኩሴ ሲሆን መጽሐፉን ያዘጋጀው የጻፈው በአምስተኛው መቶ ዓመት መጨረሻ (፭፻ ዓመት) ላይ ነው ። ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ዘውስጥ ገጽ ፪፻፳፰-፪፻፳፱)

በ ስለቤተ ክርስቲያን ሁሉ አንድነት ይጠብቁ ዘንድ አይኩሚኒቶች የተባሉት ለዓለም ሕዝበ ክርስቲያን የሚጠቅሙ ማለት የኤጲስ ቆጳሳት ጉባኤ አደረጉ ፤ በዚህም ጊዜ ለጉባኤው ስለ ቤተ ክርስቲያን ብዙ ሐሳቦች ብዙ ነገሮች ቀረቡ ነገር ግን በሐሳብ እውነተኛውን ነገር ለመሥራት አልተቻላቸውም ምክንያቱም የወንድሞቻቸውን ማለት የጉባኤውን ሐሳብ ለመስማት እንደፈለጉ ባየ ጊዜ የናትያንዝ ጎርጎርዮስ «እውነት ለመናገር ወይም በእውነት ለመሥራት ብፈልግ ከሲኖዶስ እሸሻለሁ ሲኖዶስ ሁሉ ለበጎ ነገር ለእውነት ነገር እንደተነሣ ከቶ አላየሁምና ሲኖዶስ ፀብን ክርክርን በማጥፋት ፈንታ ፀብ ክርክርን መውደድን አብዝቷልና» ሲል የተናገረው ቃል እስከ ምጽአት ድረስ ለሚነሣው ትውልድ የሚያስገርም ነው (የቤተ ርስቲያን ታሪክ ገጽ፪፻፷፰ - ፫፻፲፭)

## የሀገር ውስጥ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ

፫ኛ በእስላሞች ወረራ ምክንያት ከግብፅ ይላክ የነበረውን ጳጳስ ለማስመጣት የማይቻል መሆኑን ከተረዱት በኋላ ይህች የክርስቲያን ደሴት የሆነች አገር ያለ ጳጳስ መኖር አይገባትምና ጦርነት እስኪያቆምና መንገዱ እስኪከፈት ድረስ «ከወገናችን ሃይማኖቱ የጸና ምግባሩ የቀና ሰው መርጠን ጳጳስ እንሹም ብለው ሊቃውንቱ ሁሉ ነገሩን በጉባኤ ወስኑ በምርጫውም ጊዜ (ንጉሡም) መኳንንቱም ካህናቱም ሕቡም በአንድነት ተስማምተው ከአባታችን ከአቡነ ተክለ ሃይማኖት የሚበልጥ አናገኝም ብለው መርጠው ይደልዎ ብለው ሾመዋቸዋል ። አቡነ ተክለ ሃይማኖትም የሐዋርያነቱን ሥራ አስቀድመው ለምደውት ነበርና ቅስና ዲቁና በመሾም እየዞሩ በማስተማር አረማውያንን በማጥመቅ መንፈሳዊ ሥራቸውን እያስፋፉ ሄደዋል ከዚህ በኋላ የተዘጋው መንገዱ ሲከፈት አባ ዮሐንስ ፭ኛ የሚባለው ግብፃዊው ወር ተረኛው ጳጳስ በመጣ ጊዜ አባታችን አቡነ ተክለ ሃይማኖት የጳጳስነቱን ሥራ ይዘው መቆየታቸውን ስለሰማ አገሩ ሰፈ ነውና የቤተ ክርስቲያንን ነገር እየተማከርን አብረን እንሥራ ብሎ መልእክተኛ ላከባቸው እርሳቸው ወደ ጳጳሱ መጥተው አንተ ሳትመጣ ኢትዮጵያ በሙሉ የእኔ ነበር ። አሁን ግን አይሆንም በቃኝ ብለው በእጃቸው ያለውን አስረክበው ወደ ደብረ ሊባኖስ ሄዱ በተለይ የሚያስደንቀው አስቀድሞም ሲሾሙ በኢትዮጵያ ሊቃውንት ካህናትና ሕዝበ ክርስቲያን ይደልዎ ተብለው ያለ ጳጳስ መሾማቸው ነው ። የታሪክ መጽሐፍና ገድለ ተክለ ሃይማኖት ስንክሣር ተመልክት ።

፬ኛ ከሺህ ፪፻ ፶፯-ሺ፫፻፳፯ ድረስ በነበሩት በዓፄ ዐምደ ጽዮን ዘመን የነበረው አባ ያዕቆብ የሚባለው ግብፃዊ ጳጳስ እጨጌ ፊልጶስን ጠርቶ የሸዋ ኤጲስ ቆጶስ አድርጎ ሾሞታል ።

ገድለ ፊልጶስ ተመልከት እንግዲህ ከዚህ ላይ ልንገነዘበው የሚገባው ለሀገሩ ባዳ ለሰው እንግዳ በሆነው ግብፃዊው ጳጳስ ብቻውን የመሾም መብት ካለው በታሪክ እንዳገኘነው ኢትዮጵያዊው ፓትርያርክ እንዴት መሾም አይገባውም ?

፭ኛ በዲድስቅልያ በ፴፬ኛው አንቀጽ ጳጳስ ኤጲስ ቆጶሳትን በሚሾምበት ጊዜ ከሶስት ኤጲስ ቆጶሳት ጋር ሆኖ ይሹም ሲታጣ ከሁለት ኤጲስ ቆጶሳት ጋር ሆኖ ይሹም ካለ በኋላ ለዚህም ማስረጃ ሲሰጥ በሁለት በሶስት ምስክር ይጸናልና ። ይላል አከራካሪ ሆኖ የተገኘው ይኸው ይመስለኛል ። ነገር ግን ይህን ቃል በሐዋርያት ስም አድርገው ክብራቸውን ሊጠብቁበት ሹመታቸውን ሊያከብሩበት ደርሰውታል እንጂ ከሐዋርያት ዘመን አንስቶ እስከ ታላቁ ቆስጠንጢኖስ ዘመን ድረስ ሲኖዶስ የሚለው ጉባኤ ልዩነት የሌለበት ስለ ምሥጢረ ቤተ ክርስቲያን የሚሰበሰቡ የጳጳሳት የካህናትና የሕዝበ ክርስቲያን እንደነበረ ከገጽ ፩ ጀምሮ መመልከት ነው ሐዋርያትም ምትካቸውን በየሔዱበት ሲሾሙ በሲኖዶስ እየተሰበሰቡ ሾሙ የሚል ታሪክ ከቶ አይገኝም አንድም ሁለትም ሆነው ከራሳቸው ከሕዝበ ክርስቲያኑ መካከልኀረዩ እምውስቴትክሙ ብለው አስመርጠው ይሾሙ ነበር ስለዚህ ቤተ ክርስቲያናችንም የሐዋርያትን ሥራ መከተል አለባት እንጂ በሹመትና በክብር በሀብት በሚጣሉበት ዘመን በነገሥታት ሥልጣን የተዘጋጀውን አብነት ማድረግ የለባትም ።

ነፃነት ከሌላት ክህነት በሀገሯ
ፍጹም አይባልም የቤተ ክርስቲያን ክብሯ
በስም ብቻ መክበር ሥራውን ሳይሠሩ
የነርሱ ጸሎት ነው መቼ የማኅበሩ ተብሎ ተነግሯል ።

፯ኛ ከዚህ ላይ ለኢትዮጵያ ካህናትና ሕዝበ ክርስቲያን ላሳስብ የምፈልገው በማናቸውም ነገር ተስማምተን ራስ የሐዋሳት ሁሉ አዛዥ መሆኑን አምነን ሕዋሳችን ሁሉ ራስ ልሁን ቢሉንም እንዳይሆን ማሰብ ይኖርብናል (ማቴ. ፳፬፥፭) እናስታውስ ።

፰ኛ በአሁኑ ወቅት ማለት የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ተሐድሶ የጊዜውን ሁናቴ መልክ ተከትሎ የሚሔደውን ሕዝበ ክርስቲያን መካረው አስተምረው ወጥተው ወርደው የሚሠሩ ረዳት እንጂ ሌላ አያስፈልግምና በተረዳነው ታሪክ መሠረት እንጠቀምበት ።

መልአከ ኃይል ወ/ያሬድ መኩሪያ

ነቱ የተጐዳውን ሠራዊት አስታመዋል የሚያስፈልገውንም መድኃኒት ቀምሞና አዘጋጅቶ ለሠራዊቱ በማቅረብ ልዩ ልዩ መድኃኒት እንዲልብስ ለማይገኝ እንቆቆና መተሬ የቀጨሞ ፍሬ ሳይቀር ፈጭተውና በጥብጠው ኰሶ የሚያጠጡ በጠቅላላ በተለያዩ



ጀግናዋ ወ/ሮ ልኬለሽ በያን

የሙያ ክፍሎች የሚሰጠውን እርዳታ በመስጠት ያለባቸውን ድርሻ ማበርከታቸውን አንዘነጋውም ።

ይኸም ብቻ ሳይሆን ደግሞ ወደጠላት ጦር ሄዶ በመሰለል የጠላትን ምሽግ በመጠቆም የደከመውን በማበረታታትና ወኔ በመስጠት ወደ ጦሩ ያልሄዱትን የኋላ ደጀን በመሆንና ስንቅን በማቀበል በአድዋ ለተደረገው ጦርነት ድል ለማስገኘት ብዙ ድርሻ አበርክተዋል ።

በዚያን ጊዜ ከነበረው የእናቶች ጀግንነት የምናጤነው ነገር ቢኖር መማርና አለመማር ወይም ከልዩ የሙያ ክፍል መውጣትና አለመውጣት በሀገር ጠላት በተነሣ ጊዜ ቦታ እንደማይኖረው እና ለሀገር ከምናበረክተው ድርሻ ምንም ነገር የማያስታጉለን መሆኑን ነው በመሆኑም እናቶቻችን ቅሌን ጨርቄን ሳይሉ የተሰለፈውን ሠራዊት ተከትለው የሚፈለግባቸውን ሁሉ ያበረከቱት በዚህም የቀድሞዎቹ እናቶቻችን ያደረጉትን ሁሉ ታሪክ መዝግቦ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲያስተላልፍ ይኖራል ።

በዚህም አንፃር አሁን በቅርቡ እንደምናየውና እንደምንሰማው በተዘጋጁበት ሙያ በጠርነት ሥፍራ ተገኝተው ወይም ባሉበት ሆነው በምሥራቅና በደቡብ እንዲሁም በሰሜን የተዋጉትንና ድል ያስገኙትን የአሁኖቹን እህቶች ለጦርነቱ እርዳታ የሰጡትን የቀበሌ ሴቶች ፤ የገበሬ ሚስቶችና የወዛደሩ ሚስቶች የቀድሞዎቹ እናቶቻችን በአድዋ ካበረከቱት ባላነሰ ሁኔታ ስለአበረከቱ ታሪክ ከእነዚሁ ሴቶች ጋር ይደም ራቸዋል ። ወደፊትም ሴቶች ለሀገር እና ለወገን የሚያበረክቱት ከፍተኛ ድርሻ እንዳላቸው ተገንዝበን በመንቃትና በመደራጀት ታሪካችንን እናድሳለን ።

ወ/ት ንብረት አበበ





www.ethiopianorthodox.org

# የክርስትና እምነት እውነተኛነት

ይሆናል ወይም ይደረጋል ተብሎ በእውነተኛ የምኞት ሒደት ለሚጠበቅ ሀሊናዊ ተስፋ ወሳኝ ፍልሚያው ወይም ተግባራዊ ሚናው እምነት መሆኑ የማያወላውል ሐቅ ነው ።

በእንግሊዞች ጥቅስ ወይም የምሳሌ አነጋገር "ስለመልካሙ ተስፋ አድርግ ፤ ስለመጥፎው ግን ተዘጋጅ" እየተባለ የሚነገረው ምርምር ከዚሁ ጋር የተመሳሰለ ወይም የተያያዘ ነው ሊባል ይቻላል ።

የንግግር ስልታችንን ፈር ለማስያዝ ስንሞክርም የተግባር መሠረቱ እምነት ሲሆን የእምነት መገለጫ ደግሞ ተግባራዊ ውጤት መሆኑን የተገነዘበው ሐዋርያ "ሃይማኖት በምግባር ካልተደገፈች የሞተች ናት" ሲል የሰጠው ትምህርት አስተማማኝና ሚዛናዊ እንደሆነ እንረዳለን ።

እንግዲህ የክርስትና ትምህርት እውነተኛነቱ ሲገለጽ የኖረውና የሚኖረው በሚጨበጥና በሚዳሰስ ተግባር እንጂ እንዲሁ በዜና ብቻ አይደለም ።

ይኸንኑም በተከታታይ ለመግለፅ እንሞክራለን ። በክስተታችንም ፤ የክርስትና እምነት ተከታዮች ከገንዘባቸውና ከልዩ ልዩ ዓላማዊ ቅርሳቸው አልፈው ሥጋዊ ሕይወታቸውን ለሞት አሳልፈው መስጠታቸውንና ተአምራዊ ተግባራቸውን ከምንገነዘብበት ትክክለኛ ሒደት ላይ ስንደርስ ስለክርስትና እምነት እውነተኛነት ምንም ዓይነት ቃለ መጠይቅ አያስፈልገንም ማለት ነው።እምን፡እምን፡አይደለም፡አይደለም እንዲሁም ለራሳችሁ ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን ለሌሎች አድርጉ በሚል ዓላማ ላይ የተመሠረተው የክርስትና እምነት እውነተኛነቱ ሐቀኛ በሆነ የታሪክ ሒደት ብቻ ሳይሆን በተግባራዊ ይዘት ጭምር መሆኑ ከላይ ተገልጿል ።

በክርስትና እምነታቸው የፀኑ ሰዎች ፍርድ ሲጓደል ፤ ሕዝብ ሲበደል ፤ እውነት ከቦታው ሲታጣ ፤ ሐቀኛ ተገፍቶ ዓመፀኛ ሲቀናጣ ይቅበጠበጣሉ ። ያለ ሥጋት ያለአድልዎና ፍርሃት እንዲህ እንዲህ ሊሆን ይገባል እያሉ አንድነትን በአስከተለና በተቀናጀ ኃይል ይናገራሉ ፤ እውነት ከሚጠፋ የወለዱት ይጥፋ በሚለው ፍልስፍና ይመራሉ ።

በፍርድ ሥልጣን ላይ ከተመደቡ የክርስትና ሰዎች እንኳ አብዛኛዎቹ ይፍረድብኝ ብለው በሚሰጡት ፍርድ ከአብራካቸው የተገኙትን ልጆቻቸውን ፤ የሥጋዊ ዝምድና ተቅዋም ከሌላቸው ተከሳሾች ጋር እኩል በኩል እንደሚያስተያዩዋቸውና ሚዛናዊ ፍርድ እንደሚሰጧቸው የማይታበል ታሪካዊ ሐቅ ነው ።

ይህ መሠረታዊ ተቅዋም በግልም ሆነ በኅብረተሰብእ ዘንድ ከመጠናከሩ የተነሣ የክርስትና እምነታቸውን እውነተኛነት በልዩ ልዩ ሥቃይና መከራ ፤ ብሎም የሞትን ጽዋ በመቀበል ያስመሰከሩ አባቶች እንደነበሩ ለመጠቆም ይህ መልካም አጋጣሚ ሊሆን ይችላል ።

ወደፍሬ ነገሩ ስናመራ በእውነተኛው የክርስትና እምነት ላይ አቋማቸውን በመመሥረት ሊቀ ሐዋርያቱ ቅዱስ ጴጥሮስ ተዘቅዝቆ መሰቀሉን ፤ ቅዱስ ጳውሎስ አንገቱን ለሰይፍ አመቻችቶ መስጠቱን ከሰማዕታትም ቅዱስ ጊዮርጊስ ሰባት ዓመት ሙሉ አሠቃቂዎች የሆኑ ሥቃያትን መቀበሉንና በመጨረሻ በተሳለ ሰይፍ አንገቱን ተቆርጦ ከሕይወተ ሥጋ ወደ ሕይወተ ነፍስ መሸጋገሩን ቅዱስ እስጢፋኖስ ሥቃይ ለሚያፀኑበት ጠላቶቹ "ባለማወቃቸው ነውና ይቅር በላቸው" እያለና ወደፈጣሪው እየጸለየ በደንጊያ ተወግሮ ነፍሱን ለፈጣሪው አደራ መስጠቱን ።

ከዚህም አለፍ ብለን በየዘመኑ ከተፈጸሙትና የክርስትና እምነትን እውነተኛነት ከሚያረጋግጡት ተግባራውያን ኃይላት አንዳንዶቹን ለመጠቆም ስንፈልግ የአንዲት ክርስቲያናዊት ሴት መንፈሳዊ ተጋድሎ ትዝ ይለናል ።

ይህች ሴት የክርስትና እምነት ባልተስፋፋበት ዘመን በመገደድ ፈጣሪዋን ክዳ ለጣዖት እንድትንበረከክና እንድትሰግድ ስለተጠየቀች እንዲጋጣሚ ከፊቷ የነበረው ሽክላ ይህ ምንድነው ? ብላ ብትጠይቅ ይኸማ ሽክላ ነው ብለው ስለመለሱላት "እንግዲያውማ እግዚአብሔርም እግዚአብሔር ስለሆነ ሌላ ስም ልሰጠው ወይም ልክደው አይገባኝም" በማለቷ በታላቅ ጉድጓድ ውስጥ ለተከማቹ አንበሶች ተጥላ በሚያሰቅቅ ሁኔታ ምድራዊ ሕይወቷን አጥታለች ።

የመቶ አለቃው ፤ ልጅ ስለታመመበት እንዲያድንለት ለመድኃኒታችን ላቀረበው ልመና ከቤትህ መጥቼ አድነዋለሁ ቢለው ከዚሁ ሆነህ በቃልህ እዘዝ ልጄ ይድናል ብሎ በእምነት መናገሩ እንግዲህ ይኸንንና ይኸንን የመሳሰለው ክርስቲያናዊ ተግባር ሁሉ በእያንዳንዱ የክርስትና ሰውነት ላይ የሚያንፀባርቀው ራሱ ሃይማኖቱ እውነተኛ በመሆኑ ለሰውም ሆነ ለእግዚአብሔር ደስ የሚያሰኙ የተግባራትን ተቅዋሞች አጠንክሮና አቅፎ ስለያዘ ነው ።

ከዚህም ሌላ የክርስትናን እምነት እውነተኛነት በሒደት በይዘት በጥልቀትና በምጥቀት ረገድ የሚያረጋግጥ ሚዛናዊና ተግባራዊ ውጤት አለ ።

ይኸውም አንዱ መንፈሳዊ ሰው በሌላው ሰው የሚያሳየው ወይም እያንዳንዱ ሰው በእምነታዊ ተግባሩ የሚፈጽምለት ተአምራታዊ ተግባር ነው ።

ብዙዎች ክርስቲያኖች (ቅዱሳን) ዕውሩ እንዲያይ ፤ ደንቆሮው እንዲሰማ ፤ የታመመው እንዲፈወስ ፤ ያንካሰው እንዲረታ ፤ ለምፃሙ እንዲነፃ ፤ ይልቁንም የሞተው እንዲነሣ ማድረጋቸው በጥንቃቄ ሲታሰብና ሲመረመር የክርስትና እምነት በእውነተኛና በትክክለኛ ሒደት እንዴት ያለ ከፍተኛ ግምት ያለው መሆኑ ዓሊ የማይባል ሐቅ ነው ሊባል ይቻላል ።

ከዚህም ጋር አጣምረን የምናስላስለውና የምንገመግመው ፤ የተፈጸመ ሌላ አስደናቂ ሒደት አለ ፤ ይኸውም በመላእክት ፤ በቅዱሳን ፤ በሰማዕታት ፤ በአጠቃላይ በሃይማኖት ሰዎች ስም በፈለቀው ጠበል ለእያንዳንዱ ሕመምተኛ የሚደረገው ፈውስ ነው ።

በቅዱሳን ስም በፈለቀው ጠበል በተአምራት ጉባጦች ይቀናሉ ፤ ዕውራን ያያሉ ፤ ለረጅም ጊዜ በሕመም በአልጋ ላይ ውለው የነበሩ ሕሙማን ይፈወሳሉ ፤ አልፎ አልፎም ከአንዳንዱ ሕመምተኛ የሆድ ዕቃ ውስጥ የነበሩ እባብ እንቁራሪት ፤ ገበሎ ፤ አባ ጨጓሬ የመሳሰሉት ተንቀሳቃሾች ይወጣሉ ።

እንግዲህ የክርስትናን እምነት እውነተኛነት ለማረጋገጥ ይኸንንና ይኸንን የመሰለው ማስረጃ አጥጋቢ ሊሆን ይችላል ብለን ለመናገር እንደፍራለን ።

በመንፈሳዊ ታሪክ ረገድ የተመለከትን እንደሆነም በክርስትና እምነት የትግል ምዕራፍ ውስጥ በየጊዜው ስለሀገር ፍቅር የተፈጸሙና በይዞታቸውም የተመሳሰሉ የታሪክ ምዕራፎች እናያለን ።

ከብዙውም በጥቂቱ ለጠላት አንበረከክም ፤ ኢትዮጵያ የፋሽስቶች ቅኝ ግዛት አትሆንም ፤ ይኸንንም ትክክለኛ ሐቅ በገንዘብና በዕለታዊ ጥቅም አንለውጠውም በማለት በግፍዕ በጠላት ተደብድበው የሞቱትንና ቀዋሚ ታሪካቸው ከትውልድ ወደትውልድ በመተላለፍ ላይ ያለውን የብፁዕ አቡነ ጴጥሮስንና የደሴባቦር ክፍለ ሀገር ጳጳስ የነበሩትን የብፁዕ አቡነ ሚካኤልን የዜና ማርቆስን ገዳም አስተዳዳሪ የታላቁን ሊቅ የመምህር ወልደ ሚካኤልን በጠላት በግፍዕ የተገደሉትን የንቡረዕድ ክፍሌን ማረፍ እንዲሁም የአለቃ መርሻን ታሪክ ማስታወስ በቂ ነው ።

ይልቁንም ጀግናው ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፤ እንዲሁም የኢትዮጵያ መሬት በአጠቃላይ ለጠላት እንዳይገዙ አውግዣለሁ ብለው የኢትዮጵያ አርበኞች ከንድ በጠላት ላይ በበለጠ እንዲጠናከሩና እንዲተባበሩ ለምን ጊዜም በታሪክ ገጽ ላይ ቦታ ተሰጥቶት የሚኖር ታሪካዊ ተጋድሎ ስለፈጸሙ የክርስትና እምነትን የጥንካሬ ይዘት በሥራ ተርጉመውታል ለማለት ይቻላል ።

እንግዲህ ከላይ እንደተዘረዘረው ሁሉ የክርስትና እምነት እውነተኛነት በቅዱሳን ጥንታውያን አባቶች የተገለጸው በተአምራዊና በተግባራዊ ሁኔታዎች እንዲሁም የማናቸውም ሰው የእኩልነት መደብ ሳይጠበቅ ቀርቶ ልዩ ልዩ አሰቃቂ ግፍዕ ሲፈጸም አድራጎቱ የእምነትን ፈር ያልያዘና ያልተከተለ መሆኑን በግልጽ በመመስከር፤ከገንዘብፍቅርእንዲሁም ብዙኃኑንየኢትዮጵያ ሕዝብ በአጠቃላይ በወንድምነትና በእኩልነት ደረጃ በመመልከት ፋንታ በደካማነት መንፈስ ተመርቶ በተለይ ጉሣን ብቻ ለመሰብሰብና ለመጥቀም ከሚደረገው አሳፋሪ ሥራ ራስን በራስ በጥብቅ በመቆጣጠርና በመጠባበቅ፤ በተጨማሪም የዛሬው አብዮታችን ፍልስፍናእንደሚመራው ሁሉ ለእኔ የሚለውን የስስትና የአልጠግብ ባይነት ደባ አስወግዶ ለእኛ በሚለው መጽሐፋዊና እውነተኛ ሥራ በመመራት ይህ ታሪካዊና ባህላዊ ይዞታ በበለጠ እንዲጠናከርና በሥራ እንዲተረጎም የሚያስፈልግና በጥብቅ የሚያሳስብ ስለሆነ ሁላችንም ዓላማውን ተከትለን በተግባር እንግለጽ ።

አለቃ ዓምደ ጽዮን ተሰማ



# ሥራ የተለየው ሕይወት

ሥራ አካላትን በማንቀሳቀስ በስንፍና ጉድለት ተሳስረው የነበሩት የሰውነት ክፍሎች ስለሚፍታቱ ራሱ ሥራ በጥሩ አቅዋም ሰውነትን የሚገነባ ፤ አእምሮን የሚያድስ ፤ ሐዘንን የሚያስረሳ ፤ ብስጭትንም የሚያስወግድ የተፈተነ መድኃኒት ነው ለማለት ይቻላል ።

ባለንበት ዓለም ላይ ያለ ሥራ ሰላምና ጤና ፤ ሀብትና ብልጽግና እነዚህን የመሳሰሉትም ነገሮች ፈጽመው ሊገኙ እንደማይችሉ የታወቀ ነው ። ሕይወትም ያለ በሥራ ነው ያለ ሥራ ህልውና የለውም የሕይወት ህልውና ሊታወቅ የሚችለው ሥራ ሲኖር ነው የሕይወት ሥር ሥራ ነውና ።

ለምሳሌ አንድ ዛፍ ሥሩ ከደረቀ ቅርንጫፎቹ ለምልመው ሊያብቡ አብበውም ሊያፈሩና አጥጋቢ ምርት ሊያበረክቱ ችሎታ ስለማይኖራቸው ያላቸው ዕድል እየተሰባበሩ መውደቅ ብቻ ነው።

የዛፉ ሥር ካልደረቀ ግን በመሬት ውስጥ የሚገኙትን አልሚና ጠቃሚ የሆኑትን ማዕድናት እየሳበ ወደቅርንጫፎችም እያስተላለፈ ተፈላጊውን ምግብ ስለሚያቀርብላቸው ወር ሳይወስኑ በየጊዜው ከአበባና ከፍሬ ሳይለዩ ተፈላጊውን ምርት ሲያበረክቱ ይኖራሉ ።

እንግዲህ በዚህ አንጻር ሥራ የተለየው ሕይወትም ትርጉም አይኖረውም ማለት ነው ይኸውም የሕይወትን ህልውና የሚጠብቅ ስለ ሕይወት ህልውና የሚከታተል ሥራ ነውና ።

ነገር ግን ከዚህ ላይ ማስታወስ የሚያስፈልገን ቢኖር የዛፍ ቅርንጫፎች የሚያስፈልጋቸውን በቂ ምግብ ካላገኙ ደርቀው ከመቅረት በስተቀር ሌላ የሚጠበቅባቸው ውጤት እንደሌለ ሁሉ ፤ ሥራ የተለየው ሕይወትም እንደዚሁ ነው ።

እርግጥ ያለ ሕይወት ሥራም ቢሆን ሊሠራ አይቻልም ይሁን እንጂ ሕይወትም ያለ ሥራ የመኖር ዕድል እንደሌለው መታወቅ አለበት የሰው ልጅ የሚጠቅመውንና የሚጐዳውን መርጦ እንዲይዝ ሁለት ምርጫዎች እንደቀረቡለትና እግዚአብሔር በአንዳንድ ሰዎች ላይ አድሮ ይኸንን ሲያመለክት እንደነበርና ዛሬም ቢሆን ይህ ምርጫ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ እንደሚኖር እሙን ነው ፤ ቃሉ ዘለዓለማዊ ሕያው እንደ መሆኑ አለ ዛሬም አልተሻረም ።

ሁኖም ሕይወታቸውን የጠሉ በስንፍና የተበከሉ አንዳንድ ሰዎች ወጥተው ወርደው ራሳቸውን ረድተው ሌላውን መርዳት የሚያስችል ሙሉ ጤና እና ጠንካራ ጉልበት ሲኖራቸው ሠርቶ ማደር እንደ እሬት ስለሚዘገንናቸው የሰውን እጅ አይቶ ማደርን ይመርጣሉ ።

በዚህም መሠረት ከፍተኛ ሥራ እየመሰላቸው ሠርተውና ጉልበታቸው በሚፈቅድላቸው ራሳቸውን በመርዳት ፈንታ በልመና ዓለም ተሠማርተው በተመሳቀለ ጐዳና ተቀምጠው "ጐበዝ አትለፉኝ ስለ ሙሉ አካል እንዳንተው ነበርኩ" በማለት የሰውን እጅ እየተመለከቱ ሰው የደከመበትን እያዩ የሚኖሩ በጥቂቱ የሚገመቱ አይደሉም የሥራን ክቡርነት የሕይወትንም ምንነት የተገነዘቡ ሰዎች ግን የሰውን እጅ እየተመለከቱ መኖር ምን ያህል አሳፋሪ መሆኑን በመገንዘብ ከሥራ ሥራን ሳያማርጡ ያገኙትን ሥራ እየሠሩ ሕይወታቸውን ጠብቀው ከመኖራቸው ሌላ ቤተሰቦቻቸውን በመርዳት ወገኖቻቸውንም በማገዝ ታላቅ አስተዋጽኦና መንፈሳዊ ግዴታቸውን ሲፈጽሙ ይታያሉ ።

በዚህም መሠረት ክብራቸውን ጠብቀው ሕይወታቸውን አውቀው የምርጫቸውን ይዘት ከግቡ አድርሰው ራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን አስደስተው ይኖራሉ የእግዚአብሔርም ቃል ከዚህ የተነሣ ነው እንዲህ ሲል የምንሰማው "በፊታችሁ ሕይወትንና ሞትን በረከትንና መርገምን እንዳስቀመጥሁ እኔ ዛሬ ሰማይንና ምድርን ባንተ ላይ አስመሰክራለሁ እንግዲህ አንተና ዘርህ በሕይወት ትኖሩ ዘንድ ሕይወትን ምረጥ" ዘዳግም 30 ፣ 19 ።

ከእግዚአብሔር ቃል መረዳት እንደቻልነው እያንዳንዱ ሰብአዊ ፍጡር ሕይወትን እንጅ ሞትን መምረጥ የለበትም መንፈሳዊ ክብርን እንጅ አደጋ የሚያስከትለውን ስንፍና መከተል አያስፈልግም በጠቅላላ የሚጐዳበትን ጐዳና ሳይሆን የሚድንበትንና ሕይወት የሚያስገኝበትን ጐዳና መራመድ ይኖርበታል ።

እዎ ሥጋዊ አካል እንደምናየው በሥጋና በደም ፤ በጅማትና በአጥንት ተያይዞና ተገጣጥሞ በመኖሩ ነው ጸንቶ የሚኖረው ግን ከእነዚህ ከላይ ከተጠቀሱት አራት ነገሮች ማለት ከሥጋና ከደም ከጅማትና ከአጥንት አንዱ ጐድሎ ከተገኘ ሁሉም እንደማይፈርሱ አያጠራጥርም ።

እንግዲያስ በመንፈሳዊ ሥራ ያልተገነባ ሰብአዊ አካል (ሰውነትም) ሕይወት አለው ለማለት አያስደፍርም ምክንያቱም ሥጋዊ አካል አካላትን የሚገነቡ ገምቢ ምግቦች እንደሚያስፈልገው ሁሉ በመንፈሳዊ ሥራ ያልተገነባም ህልውና ከህልውና ሊቆጠር አይችልም መንፈሳዊ ሕይወት አልተጨመረበትምና ስለዚህ መንፈሳዊ ሥራ የተሞላበት ሕይወት እንጅ ሥራ የተለየው ሕይወት ስልጥኖብን እንዳይኖር መገንዘብ አለብንአለኝታችንሕይወታችንነውና።

ክነፈርግብ ማርቆስ



www.ethiopianorthodox.org

# ተክሊል ያለ ቁርባን ?

ጽንዓት ላለው ሕጋዊ ጋብቻ መሠረት የሚሆነው ቁርባን ከተክሊል ጋር ሲሆን እንጂ ተክሊሉ ብቻውን ስለተደረገ የተሟላና የተስተካከለ አይሆንም ። ሲሉ የቤተ ክርስቲያን ምሁራን ይናገራሉ ።

በብዙዎቻችን ዘንድ ግን ቁርባን ተገንጥሎ ተክሊል ለፎቶ መነሻ እየሆነ መሄዱ አዘውትሮአል ። ብዙዎቹ ተክሊሉን ብቻ የሚያደርጉት ለሚደረገው ሥርዓተ ፀሎትና ለወደፊቱም የመሠረቱት ጋብቻ ጽናት እንደሚኖረው አምነውበት ሳይሆን እንዲያው ለይስሙላና ከላይ እንደተጠቀሰው ለፎቶ ማንሻ መሆኑ አይጠረጠርም ። ጽናት እንዲኖረውማ ከተፈለገ ዋናውን ክፍል የያዘው ቅዱስ ቁርባን ተገንጥሎ መቅረት የለበትም ነበር ። የዚህ ዓይነቱ አካሄድ አሁንም እየቀጠለ ከሄደ ለብዙዎች የጋብቻ ሕይወት መሰናክል ሳይሆን አይቀርም ፤ ከሁኔታዎቹ እንደምናየው ተክሊሉን ብቻ አድርገው የሚሄዱት ብዙዎቹ አለመኖች ወይም ስለዕምነት ግድ የለሾቹ ናቸው ከዚህም ሌላ ራሳቸው የቤተ ክርስቲያን አማኞችና እንዲሁም አገልጋዮችም መካከል በዚሁ ሁኔታ ኑሮአቸውን የመሠረቱ አሉ በዚህ ስህተታዊ ድርጊት ውስጥ እንግዲህ አማኞቹም አለመኖችም አሉበት ፤ ይኸ ዓሌ የማንለው የአደባባይ ምሥጢር ነው ። ሐዋርያው ያዕቆብ በመልእክቱ ዕምነት ያለሥራ ሥራ ያለዕምነት የሞተች ናት ብሎ እንደተናገረው እምነታቸውን በሥራ ወይም በሕይወታቸው አካሄድ የማይተረጉሙት በጠቅላላው ዓላማ የለሾች የሆኑት አማኞች ነን ባዮች ወይም መሳዮች ሁኔታ ያሳዝናል ። ለሌሎች በምሳሌነት እራሳችንን በበጐ ነገር ልናሰማራ ሲገባን በማይገባ ምሳሌ አካሄዳችንን እናሳውቃለን በዚህ ለሌሎች የመሰናክል ዓለት ከመሆን አናልፍም ማለት ነው ። ተክሊል እንግዲህ ብቻውን የፀና አይሆንም ካልን ሁላችንም ቢሆን ከተክሊል ጋር የሚካሄደውን ሥርዓት አውቀን እንዳላወቅን ማለፍ በእራሳችን የጋብቻ ሕይወት ላይ የቀልድ ዘመቻን ማካሄድ ነው ዓላማችን ለማስመሰል ወይም ለጌጥ ብቻ ከሆነ በውስጡ ያለውን ምሥጢርና የፀሎት ሂደት ለማሟላት ፈቃደኞች አለመሆናችን በጋብቻ ሕይወታችን ላይ አንድ ዓይነት ያልተስተካከለ የጥርጣሬ ጉዳና እንዳለ እንገልጻለን ። በዚህም ዋነኛው ክፍል ላይ ፈፀም ይቀራል ።

እንግዲህ የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት እንደፈለግን የምንበታትነውና የምንገነጣጥለው ከሆነ የእምነታችን ትርጉም ወይም ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄደን የምናደርገው ዓላማችን ግልጽ አይሆንም ፤ የባሰውን ሕይወታችንን በጥርጣሬ ውስጥ እንዲገባ እናስገድደዋለን ስህተቱ ጐልቶ የሚታየው አሁን አማኞች በተለይ አገልጋዮች በሆኑት ላይ ነው ስህተታዊ ድርጊታቸውን ለተከታዮቻቸው አንፀባርቀዋልና ።

በትክክል የተዘጋጀውን የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ለእራስ አካሄድ እንዲመች ሕጋዊ የሆነውን ሥርዓት ማጉደልና መገነጣጠል ኑሮአችንን ለመወሰን ያለብን ችግርና ጥርጣሬ እንዳለ አጉልቶ ያሳያል ይኸ በአድራጊዎቹ በኩል የሚታይ እውነት መሳይ ፍጹም ስህተት የሆነ ድርጊት ሲሆን በቤተ ክርስቲያንም በኩል እንዲሁ ሳታርምና በግድ የለሽነት የመጡላትን ሁሉ ልክ ነው በማለት አገልጋዮቿን እንኳ ሳይቀር በስህተት ጉዳና ስትመራ ቅርም አይላት ለመሆኑ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ጸሎት ከተፈፀመ በኋላ መጥቶ ተክሊል ብቻ ማድረግ ትክክለኛነቱ ጐልቶ ስለማይታይ ይኸ እራሱ ጉድለት እንዳለበት ያሳየናል ።

በጠቅላላው ምሁራን እንደሚሉት ዋናው ክፍል ሕጋዊ የሚያደርገውና የሚያስተሳስረው ቅዱስ ቁርባን ነው ። ተክሊሉ ብቻውን ግን ከቁርባኑ ጋር የሚደረገውን ያህል ሕጋዊነትና ጽናት የለውም እንዲያው ለወገን (ለታይታ) ካልሆነ በስተቀር ለብቻው ማድረግ በአንድ እጅ ለማጨብጨብ መሞከር ወይም እንደ ጊዜያዊ ሃሳብ ይቆጠራል ። እንግዲህ ተክሊል ብቻውን ከሆነ ከሕገወጡ ጋብቻ ብዙ ልዩነት ወይም የተሻለ ነገር የለውም ለማለት ይቻላል ምክንያቱም ሙሉ ያልሆነ ነገር ጉድለት ስለአለበት ነው ። ስለዚህ ሕይወታችንን ያለ ጉድለት ያለመጠራጠር ለማስኬድ ሙሉ የሆነውን ቅዱስ ቁርባን እናጓድል ።

ንብረት አበበ

# የወንጌል አዳራሽ

ከገጽ ፲፮ የዞረ

ዝሙራቸው በተለይም ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ ከግዕዝ ልሳን ጋር እያቀናጀ በማቅረብ በያሬዳዊዜማዎቹለሰሚዎች አስደናቂ መስሎ ይታያል ።

ማኅበሩ ከሌላ ተመሳሳይ ማኅበራት ጋር ያለው ክርስቲያናዊ ግንኙነቱ፡ የገቢና የወጪ የደብዳቤ ማኅደራቱ፡ ቋሚ ምስክሮች ናቸው ቢሆንም ማኅበሩ አንዳንድ ችግሮችን የሚያስወግድለት ከቶ አላገኘም ምንም እንኳን መንፈሳዊ ቢሆንም መዝሙርና የልብስ መሣሪያዎች እጅግ ያስፈልጉታል ብለን እንገምታለን ፤ ማንም ክርስቲያናዊ ዜጋና ድርጅት ይህን የጌታ ማኅበር በቀላሉ ማየት የለበትም ስለሆነም መንፈሳዊ ክርስቲያናዊ ማኅበራት በተለይም በአዲስ አበባ የሚገኙና በወንጌል ማኅበርተኛ እሆን ዘንድ ስለወንጌል የሚገባኝን ሁሉ አደርጋለሁ በሚል ሐዋርያዊና ክርስቲያናዊ መርሆ የሚመሩ ግለሰቦችና ድርጅቶች ሁሉ ለከሣቴ ብርሃን ሰላማ ስብከተ ወንጌል ማኅበር የፖ.ሣ.ቁ. 53 መቀሌ ብለው ጠቃሚ ዕርዳታና ክርስቲያናዊ የሞራልና የማቴሪያል ድጋፍ ይሰጡት ዘንድ ለክርስቲያን ድርጅቶች ሁሉ በማኅበሩ ስም እጠይቃለሁ ።

ከአባላቱ አንዱ
ግርማይ ኃይሉ



# ይህን ያውቁ ኖሯልን ?

ከእጅጉ ረታ

በቁጥር 15 ትንሣኤ መጽሔት ላይ በዚህ ባለንበት በሐያኛው ምዕተ ዓመት እመቤታችን በልዩልዩጊዜና ቦታ ተገልጻ መታየቷን ከብዙው በጥቂቱከአንድየ ውጭ ሐገር መርጬናተርጉሜ ማቅረቤ ይታወሳል ። አሁንም እንደዚሁ በ19ኛው ምዕተ ዓመት ከአንድ ይልቅ ፤ ከሁለትና ከዚያ በላይ ለሆኑ ሰዎች የተገለጠችበትንና የታየችበትን በመምረጥ ለአንባቢዎቼ እነሆ አቅርቢአለሁ ። ይህንንም ከአንድ በላይ ለሆኑ ለብዙ ሰዎች ተገልጣ መታየቷን መርጬ ያቀረብኩት ያለ ምክንያት አይደለም ። ማናቸውም ነገር በሁለትና በሦስት ሰዎች ምስክርነት የተረጋገጠ ከሆነ የታመነ መሆኑ በመጽሐፍ ስለተጻፈ ይህንኑ አንባቢዎቼ ይገነዘቡታል ብዬ ተስፋ በማድረግ ነው ።

በሚቀጥለው መጽሔት ደግሞ ወደ አለፉት ዘመናት ማለትም ወደ 18ኛውና 17ኛው ምዕት ዓመታት በማለፍ የተገለጠችባቸውንና የታየችባቸውን ጊዜና ቦታዎች ለማቅረብ እሞክራለሁ ። ከዚያም እንዲሁ እያለ ወደ አለፉት ዘመናት ይቀጥላል ማለት ነው ። እንግዲህ ይኸውላችሁ ታሪኩ ።

1) በ19 9 1846 ዓ.ም. በፈረንሳይ ሀገር ላ. ሰሌት በተባለች ቦታ ማክሲም ጂራድና ሜላኒ ካልቫ ለተባሉ ለ11 እና ለ15 ዓመታት ልጆች እመቤታችን እንደ ጸሐይ የሚያበራ ብሩህ ልብስ ለብሳ ተገልጻ አነጋግራቸዋለች ።

2) በ23 6 1848 ዓ.ም. በፈረንሣይ ሀገር ሉርድ አጠገብ በምትገኝ ምንሲ በተባለች መንደር ነዋሪ ለሆኑ 11 ሰዎች እመቤታችን ደጋግማ ተገልጻ ታይታቸዋለች ።

3) በ11 6 1849 ዓ.ም. በእስትሪያ ውስጥ ዶሲና በተባለች ቦታ ሦስት እረኞች ብዙ ጊዜ ተገልጻ አይተዋታል ።

4) በ22 7 1856 ዓ.ም. በኢጣልያ ሀገር አሲሲ ውስጥ ማሪዮ ፍሬድሪክ የተባለች ወይዘሮ ከህመሟ በተአምር ከዳነች በኋላ እመቤታችን በመላእክት ታጅባ ተገልጣላታለች ።

5) በ13 1 1868 ዓ.ም. በቼኮዝላቫክያ ውስጥ በፊል ፕሶዶርፍ ነዋሪ የሆነች ማግደሊና ኬድ የተባለች የ30 ዓመት ወይዘሮ ግቢ ነፍስ ውጭ ነፍስ ይዟት ስታጣጥር እመቤታችን ተገልጻ ከደዌዋ ፈውሳ ከሞት አፋፍ መልሳታለች ።

6) በ15 8 1871 ዓ.ም. በፈረንሳይ ሀገር ዊልሸብር ላይ ባርባራ ኩኖራድ የተባለች የ (9) ዓመት ልጅ እመቤታችን ደጋግማ ከተገለጠችላት በኋላ ወዲያውኑ ከሕመሟ ለመዳን በቅታለች።

7) በ25 8 1811 ዓ.ም. በዩ ኤስ.ኤ. ሉዊስ ውስጥ እመቤታችን ነጭ ልብስ ለብሳ የከዋክብት ቅርጽ ያሉበት የወርቅ አክሊል ደፍታ በመገለጥ ቲሬዛ ሸፈር የተባለችውን ወይዘሮ ከሞት አፋፍ አድርሷት ከነበረው ሕመም እንድትፈወስ አድርጋታለች ።

8) በ17 3 1873 ዓ.ም. ዊሂትልሼይም አልሴስ በፈረንሳይ ሐገር ከሕፃንነት እስከ ሽበት ባለው የእድሜ ደረጃ ለሚገኙ አያሌ ሰዎች እመቤታችን በመደጋገም ተገልጣ ለብዙ ጊዜ ታይታችዋለች ።

9) 14 4 1873 ዓ.ም. በፈረንሳይ ሀገር ኤልሴክ ውስጥ ኡልባች በተባለች መንደር እመቤታችን ለብዙ ሰዎችና በተለይም ዮሴፍ ሆፈር ለተባለ ሰው ተገልጣ ንስሐ እንዲገቡና እዘውትረውም እንዲጸልዩ ነግራቸዋለች ።

10) በ27 6 1877 ዓ.ም. በፖላንድ ሀገር ዲሽዎልድ በተባለ ቦታ አራት በልዩ ልዩ የዕድሜ ክልል ውስጥ ለሚገኙ ሴቶች በብሩህ ደመና ተከባና መላእክት አጅበዋት ለረጅም ጊዜ ተገልጻ ታይታቸዋለች ።

11) በ8 5 1890 ዓ.ም. በፈረንሳይ ሃገር ሲፒ በተባለች ቦታ እመቤታችን በብርሃን ደመና ተከባ ፤ መላእክት ረጅም መጋረጃ ይዘው እጆቿን በትእምርተ መስቀል አመሳቅላና በአርምሞ ሆና አልፍሬድና ማርዮ ካሊዮ ለተባሉ ልጆች ተገልጣ ታይታቸዋለች ።


12) በ18 3 1896 ዓ.ም. ቲሊ ሱር ሱዌ ውስጥ ፈረንሳይ ሀገር ለ50 የትምህርት ቤት ሕጻናት ከመላእክትና ከቅዱሳን ጋር ተገልጣ ታይታቸዋለች ።

(ይቀጥላል)



www.ethiopianorthodox.org

# እውነተኛ ጾም



በኃይልህ ፡ ጨክነ ፡ አትጮኽ ፡ ድምፅህን ፡ እንደ መለከት ፡ አንሣ ፡ ለሕዝቤ ፡ መተላለፋቸውን ፡ ለያዕቆብ ፡ ቤትም ፡ ኃጢአታቸውን ንገር። ነገር ፡ ግን ዕለት ፡ ዕለት ፡ ይሹኛል ፡ መንገዴንም ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ፡ ይወድዳሉ ፡ ጽድቅን ፡ እንዳደረገ ፡ የአምላኩንም፡ ፍርድ ፡ እንዳልተወ ፡ ሕዝብ ፡ እውነተኛውን ፡ ፍርድ ፡ ይለምኑኛል ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ለመቅረብ ፡ ይወድዳሉ ። ስለ ፡ ምን ፡ ጾምን ፡ አንተም ፡ አልተመለከትኸንም ? ሰውነታችንንስ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አዋረድን ፡ አንተም ፡ አላወቅህም ? ይላሉ ። እነሆ ፡ በጾማችሁ ፡ ቀን ፡ ፈቃዳችሁን ፡ ታደርጋላችሁ ፡ ሠራተኞቻችሁንም ፡ ሁሉ ፡ ታስጨንቃላችሁ ። እነሆ ፡ ለጥልና፡ ለክርክር ፡ ትጾማላችሁ ፡ በግፍ ፡ ጡጫም ፡ ትማታላችሁ ፡ ድምፃችሁንም ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ታሰሙ ፡ ዘንድ ፡ ዛሬ ፡ እንደምትጾሙት ፡ አትጾሙም ። እኔ ፡ የመረጥሁት ፡ ጾም ፡ ይህ ፡ ነውን ? ሰውስ ፡ ነፍሱን ፡ የሚያዋርድበት ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ቀን ፡ ነውን? ፡ በውኑ ፡ ራሱን፡ እንደ ፡ እንግጫ ፡ ዝቅ ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ ማቅንና ፡ አመድንም ፡ በበታቹ ፡ ያነጥፍ ፡ ዘንድ ፡ ነውን? በውኑ ፡ ይህን ፡ ጾም ፡ ለእግዚአብሔርም ዘንድ ፡ የተወደደ ፡ ቀን ፡ ትለዋለህን ? እኔስ ፡ የመረጥሁት ፡ ጾም ፡ ይህ ፡ አይደለምን? የበደልን ፡ እስራት ፡ ትፈታ ፡ ዘንድ፡ የቀንበርንስ ፡ ጠፍር ፡ ትለቅቅ ፡ ዘንድ ፡ የተገፉትንስ ፡ አርነት ፡ ትሰድዱ ፡ ዘንድ ፡ ቀንበሩንስ ፡ ሁሉ ፡ ትሰብሩ ፡ ዘንድ ፡ አይደለምን? እንጀራንስ ፡ ለተራበ፡ ትቈርስ ፡ ዘንድ ፡ ስደተኞቹን ፡ ድሆች ፡ ወደ ፡ ቤትህ፡ ታገባ ፡ ዘንድ ፡ የተራቈተውንስ ፡ ብታይ ፡ ታለብሰው፡ ዘንድ ፡ ከሥጋ ፡ ዘመድህ ፡ እንዳትሸሸግ ፡ አይደለምን? የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ብርሃንህ ፡ እንደ ፡ ንጋት ፡ ይበራል ፡ ፈውስህም ፡ ፈጥኖ ፡ ይበቅላል ፡ ጽድቅህም ፡ በፊትህ ፡ ይሄዳል ፡ የእግዚአብሔርም ፡ ክብር ፡ በኋላህ ፡ ሆኖ ይጠብቅሃል ። የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ትጠራለህ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ይሰማሃል ፡ ትጮኻለህ ፡ እርሱም፡—እነሆኝ ይላል ። ከመካከልህ ፡ ቀንበርን ፡ ብታርቅ ፡ ጣትህንም ፡ መጥቀስ ፡ ብትተው ፡ ባታንጐራጕርም ፡ ነፍስህንም፡ ለተራበ ፡ ብታፈስስ ፡ የተጨነቀውንም ፡ ነፍስ ፡ ብታጠግብ ፡ ብርሃንህ ፡ በጨለማ ፡ ይወጣል ፡ ጨለማህም ፡ እንደ ፡ ቀትር ፡ ይሆናል ። እግዚአብሔርም ፡ ሁልጊዜ ፡ ይመራሃል ፡ ነፍስህንም ፡ በመልካም ፡ ነገር ያጠግባል ፡ አጥንትህንም ፡ ያጠናል ፡ አንተም ፡ እንደሚጠጣ ፡ ገነት ፡ ውኃውም ፡ እንደማያቋርጥ ፡ ምንጭ ፡ ትሆናለህ ። ከዱሮ ፡ ዘመን ፡ የፈረሱት ፡ ስፍራዎች ፡ ይሠራሉ ፡ የብዙ ፡ ትውልድም ፡ መሠረት ፡ ይታነጻል ፡ አንተም፡—ሰባራውን ፡ ጠጋኝ ፡ የመኖሪያ ፡ መንገድን፡ አዳሽ ፡ ትባላለህ ።

ኢሳ. ፶፰ ፡ ፩—፲፪


**የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር**

የፖ. ሣ. ቁጥር 30750
ስልክ 122033
አዲስ አበባ

የፖ. ሣ. ቁጥር 700
ስልክ 113455
አሥመራ




# ኢ.ኦ.ተ.ሐ.ድ

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፣ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፡ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።


የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት

ስልክ ቍ. 116616
የመል. ሣ. ቍ. 3137
አዲስ አበባ


www.ethiopianorthodox.org